በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የገቢ ሂሳብ፣

1. ዩኒቨርስቲው ውስጥ ከተከራዩት ሰባቱ ማህበራት በውላቸው መሰረት በየወሩ የሚጠበቅባቸውን ወርሃዊ ኪራይ በድምሩ ብር 61,159.00 ያልተሰበሰበ መሆኑን፣

<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

2. ዩኒቨርሲቲው በድም ብር 38,062.00 አላግባብ ከውሎ አበል መመሪያው ውጭ በብልጫ የከፈለ መሆኑን፣
3. ዩኒቨርሲቲው በምስራቅ ጉጂ ዞን ሊበን ወረዳ ቡራ ደራ ቀበሌ የአካባቢ ጥበቃ ስራ ለሰሩ ለ144 ሰዎች ለእያንዳንዳቸው የ15 ቀን በቀን ብር 50.00 ሂሳብ እንዲከፈላቸው በማለት በድምሩ ብር 108,000.00 ለተቋሙ ላልተሰራ ስራ ከመንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ውጭ ለዩኒቨርስቲው ከተበጀተለት በጀት ላይ የተከፈላቸው መሆኑን፤
4. ዩኒቨርስቲው በድምሩ ብር 1,443,461.26 የዕቃ ግዥን እና የአገልግሎት ክፍያን አገልግሎቱን ባገኘበት በበጀት ዓመቱ መክፈል ሲገባው ለዩኒቨርሲቲው ከተበጀተለት የ2009 በጀት ዓመት ላይ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን፣
5. ዩኒቨርስቲው በድምሩ ብር 333,145.00 የአበል መጠየቂያ ሳይቀርብ፣ ያለማስረጃ እና ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ የውሎ አበል የተገኘ መሆኑን፣
6. ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመዋዋል ግዥ ሲፈጽም በውሉ ጊዜ ባለማቅረባቸው በድምሩ ብር 3,444,690.21 የጉዳት ካሳ ቀንሶ ማስከፈል ሲገባው ሙሉ ክፍያ የከፈለ መሆኑን፤
7. በድምሩ ብር 10,165,685.61 ወጪዎች በተገቢው የሂሳብ መደባቸው ሳይመዘገቡ የተገኙ መሆኑ፣
8. በድምሩ ብር 576,042.45 የወጪ ደረሰኝ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን፣
9. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 4,606,950.93 የመኪና ጎማ፣ ኮምፒዩተሮች እና የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ በዋጋ የማቀረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈፅም አንድ አምራች ድርጅትን የንግድ ስም በመጥቀስ ብሪጅስቶን ወይም ተመሳሳይ ጥራት ያለው በማለት ከመመሪያ ውጭ ግዢ የፈጸመ መሆኑን፣
10. ዩኒቨርሲቲው የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በተዋዋለው በማዕቀፍ ስምምነት ውል መሰረት ኮምፒዩተሮችን ባለመግዛቱ በድምሩ ብር 12,162,380.00 የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ በብልጫ እንዲወጣ ማድረጉን፣

11. ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ልዩ ልዩ ውል ፈጽሞ ድርድቶቹ በውሉ መሠረት ባለመፈጸማቸው ሊሰበስብ የሚገባ የጉዳት ካሣ በድምሩ ብር 10,057,217.40 ያልሰበሰበ መሆኑ፣

<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

12. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር **13,066,694.56** የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ እና በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

<u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

13. በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ከሚታይ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በድምሩ ብር 515,142.50 መወራረድ ሲገባ ከአንድ ዓመት በላይ መቆየቱን፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 13 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት ዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣</u>

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ በጀት የሚገዛው የተማሪዎች የምግብ ግብዓት እና ዕቃ በየቀኑ በተዘጋጀ የርክክብ ቅጽ በየቀኑ በትክክል ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን፣ ቆጥሮና አስመዝኖ በየእለቱ ተፈራርሞ ማስገባት ሲኖርበት የብር 3,659,245.43 የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴው ሳይፈራረም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ በማድረግ ብቻ ለአቅራቢዎቹ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው ግዥ ሲፈጽም ከዕቃ ጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴዎች (ከባለሙያዎች) ስለትክክለኛነቱ ማስረጃ ሳይቀርብ የብር 4,359,605.44 ንብረት ክፍል ገቢ ተደርገው ክፍያ ለአቅራቢዎች የተፈጸመ መሆኑን፣

- ዩኒቨርሲቲው የብር 40,645,567.80 ግምት ያላቸው ዕቃዎች ግዥ ሲፈጸም የግዢ ማስታወቂያውም ሆነ አሸናፊ አቅራቢ ድርጅቶችን በኤጀንሲው ዌብ ሳይት አማካኝነት ለህዝብ ይፋ እንዲሆን አለመደረጉን፣
- ዩኒቨርስቲው ከኤቨር ሻይን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ጋር የላብራቶሪ ዕቃዎችንና ኬሚካሎችን ለመግዛት ውል የተዋዋለ ሲሆን በውሉ ላይ ውሉን የተፈራረሙበት ቀን እና አቅራቢው አቅርቦቱን የሚጀምርበትና የሚያጠናቅቅበት ቀን ሳይጠቀስ፣ ብር 309,049.74 የከፈለ መሆኑን፣
- ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተመደበው የወጪ በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር በየፕሮግራሞቹ ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 1,577,288.80 ያልተሰራበት በጀት መገኘቱን፣

<u>ሌሎች ጉዳዮች፣</u>

- በአጠቃላይ የዩኒቨርስቲው የንብረት አስተዳደር ሲታይ በንብረት ደንብና መመሪያ መሠረት ዕቃዎች በአግባቡ ያልተያዙና ያልተወገዱ እንዲሁም የተዘረጋ የንብረት ቁጥጥር ስዓርት ባለመኖሩ ለረዥም ጊዜ በመቀመጣቸው ለብክነት እየተዳረገ መሆኑን፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-17353 ታታ አውቶቡስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-16646 ሳን ሎንግ አውቶቡስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-21246 ሳን ሎንግ አውቶቡስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-17625 ሚኒ ባስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-17393 ሚኒ ባስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-16653 ቶዮታ ላንድ ክሩዘር፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-16692 ፒክ አፕ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-16693 ፒክ አፕ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-16687 ፓጃሮ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-2100, 2101እና 2102 ሞተር ሳይክሎች ብዛት 12 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌላቸው መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው ካሉት 36 ተሽከርካሪ መኪናዎች እና 11 ሞተር ሳይክሎች ውስጥ በኪ/ሜትር የሚጠቀሙት ነዳጅ ከልኬቱ ጋር ሲመዛዘን 15 ተሽከርካሪ በመብለጥ እና 14 ተሽከርካሪ በማነስ የሚያሳይ በመሆኑ ልኬቱን በትክክል እንደማይሰራ የተገኘ መሆኑን፣

- **የሰሌዳ ቁጥር** 4-16021 **ዳም አውቶቡስ የሰሌዳ ቁጥር** 4-1221 **ሞተር ሳይክል የሰሌዳ ቁጥር** 4-2102 **ሞተር ሳይክል የነዳጅ መቁጠሪያ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ ታውቋል፡፡**
- በ2008 የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ እየተወሰደ አለመሆኑን፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>የገቢ ሂሳብ፣</u>

1.1 <u>ግኝት፣</u>

የፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል 4 የመንግስት ገቢ አሰባሰብና ወደ ተጠቃለለ ፈንድ ገቢ ስለማድረግ የመንግስትን ገቢ በአግባቡ በመሰብሰብና ወደ ተጠቃለለ ፈንድ ገቢ ማድረግ እንደሚገባ በመመሪያው የተገለፀ ቢሆንም ዩኒቨርስቲው በግቢው ውስጥ የሚገኙትን ለንግድ እና ለመዝናኛ አገልግሎት የሚሆኑ ክፍሎችን ለተለያዩ ማህበራት በውል ያከራየ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ከዩኒቨርስቲው ከተከራዩት ሰባቱ ማህበራት በውላቸው መሰረት በየወሩ የሚጠበቅባቸውን ወርሃዊ ኪራይ በድምሩ ብር 61,159.00 ያልከፈሉና ዩኒቨርስቲው ተከታትሎ ያልሰበሰበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

1.2 <u>ስጋት፣</u>

መንግስት ለገቢ ማመንጫ ብሎ ላወጣው ወጭ ተመጣጣኝ ክፍያ ማግኘት ሲገባው ላያገኝ ይችላል፣ የመንግስት ገቢ ለብክነትና ለምዝበራ ሊዳረግ ይችላል፡፡ እንዲሁም ዩኒቨርሲቲው ከውስጥ ገቢ በመሰብሰብ ሊሰራቸው ያቀዳቸውን ስራዎች ሊያስተጓጉል ይችላል ፡፡

1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማህበራቱ በገቡት ውል መሰረት ወርሃዊ የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ የማይከፍሉም ከሆነ በውላቸው መሰረት ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ሳይሰበሰብ የቀረው የኪራይ ገቢም ተሰብስቦ ለዩኒቨርስቲው ገቢ ሊደረግና ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ከተከራዮች ላይ የሚፈለግባቸው የክራይ ዋጋ እንዲሰበሰብ ተደርጓል የገቢ ደረሰኝ አያይዘናል በቀጣይም የሚመለከተው የስራ ክፍል ክትትል እያደረገ በውሉ መሰረት ገቢ እንዲደረግ ይሰራል፡፡

1.1.5 የኦዲተሩ አስተያት፣

እንዲሰበሰብ ተደርጓል የገቢ ደረሰኝ አያይዘናል ተብሎ ምላሽ ለተሰጠው የቀረበ የገቢ ደረሰኝ እንደሌለ መግለጽ እንወዳለን፡፡

2 የወጪ ሂሳብ፣

2.1.1 ግኝት፣ በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል፣

የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ ሰኔ /2004 ዓ.ም ክፍል 2 የውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ውጭ ወደ ሌላ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ እለቱን መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳና እራት በተመገበባቸው የክልላዊ ከተማ፣ የዞን ከተማ፣ የወረዳ ከተማና የከተማ አስተዳደሮች እንዲከፈል የተመደበውን አበል ለእያንዳንዱ ቀን እንደሚከፈል ይገልፃል፡፡ ነገር ግን ከጅማ ዩኒቨርስቲው በቁጥር ጀዩ105/1170 በቀን ሰኔ 16/2008 ዓ.ም ስልጠና እንደሚሰጥና የሚቆይበትንም ጊዜ ሲገልፅ ለ15 እና ለ30 ቀናት እንደሚቆይ በተፃፈዉ ደብዳቤ ገልጧል፡፡ ሆኖም ግን ለዩኒቨርስቲው ሰራተኞች የውሎ አበል ሲከፍል፣

- ከአይሲቲ ዳይሬክቶሬት ስልጠናዉ ለ30 እና ለ45 ቀናት እንደሚቆይ እና ለ7 ሰራተኞቹ አበል እንዲፈቀድላቸዉ የጠየቀና የተከፈላቸው ሲሆን ስልጠናዉን የሚሰጠዉ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከጠቀሰዉ ጊዜ በማስበለጥ በቀን 30/11/2008 በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0867747 ለእያንዳቸዉ የ15 ቀን አበል በድምሩ **ብር 16,095.00** በብልጫ መከፈሉን፣ ዝርዝሩን አባሪ 2 ላይ ይመልከቱ፡፡
- ጨረታ ለመክፈት ወደ አ/አ ለሚሄዱ 10 ሰራተኞች ፈቃድ የተሰጠ ቢሆንም በቀን 13/05/09 በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0851554 ክፍያ የተፈፀመዉ ግን ለ13 ሰራተኞች ብር 37,596.00 ሲሆን ለሶስት ሰራተኞች አበል ሳይፈቀድ ብር 7,554.00 የተከፈለ መሆኑ እና በተጨማሪም ከነዚህ 13 ሰራተኞች ውስጥ ለ3 ሰራተኞች በአዲስ አበባ የአበል ክፍያ በመካከለኛ አበል በብር 165.00 ሂሳብ መከፈል ሲገባዉ በከፍተኛ አበል በብር 206.00 ሂሳብ በመከፈሉ በብልጫ ብር 1,845.00 በልዩነት የተከፈለ በመሆኑን፣ በድምሩ ብር 9,399.00 አላግባብ የአበል ክፍያ የተከፈለ መሆኑ

እና በተጨማሪም መንግስት ባወጣው የውሎ አበል የመወራረጃ ቅጽ ወጪ የተደረገዉ ሙሉ የአበል ገንዘብ ማለትም 37,596.00 እስከ 12/11/09 ድረስ አበሉ ሳይወራረድ ነገር ግን በወጪ የተመዘገበ መሆኑን፣ ዝርዝሩን አባሪ 3 ላይ ይመልከቱ፡፡

- የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሰራተኞች ከቀን 11/05/09 እስከ 16/05/09 ለስብሰባ ወደ ሃዋሳ እና አዲስ አበባ እንደሚሄዱ ገልፀዉ ለአስተዳደር እና ልማት ም/ፕ/ጽ/ቤት አበል እንዲሰራላቸዉ ጠይቀዋል፡፡ ነገር ግን ዩኒቨርስቲዉ ከላይ ከተጠቀሰዉ መመሪያ ውጭ በቀን 30/05/09 በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0859919 አበል ሲከፍል ከ11/05/09 እሰከ 16/05/09 በአዲስ አበባ እና ሃዋሳ እንደሚቆዩ እየታወቀ የተጠየቀው የ6 ቀን ሲሆን ከተባለዉ ቀን በላይ የ16 ቀን አበል በመሰራቱ፣ በድምሩ ብር **12,568.00** በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤እና የአንድ ሰራተኛ የአብረሃም ብሳዋ እስከ 12/11/09 ድረስ ያልተወራረደ መሆኑ፤ ዝርዝሩን አባሪ 4 ላይ ይመልከቱ፡፡

በድምሩ ብር **38,062.00** አላግባብ በብልጫ የተከፈለ የውሎ አበል መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

2.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- መንግስት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡
- የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- ከህግ እና መመሪያ ውጭ በመወሰን የሚከፈል ክፍያ ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡

2.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በብልጫ ወይም ያለ አግባብ የተከፈለዉ ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ተደርጎ ሪፖረት ሊቀርብ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተወራረዱ በሚል የተያዙ ወይም የታለፉ ሂሳቦች በድጋሚ ህጉ እና መመሪያዉ በሚያዝዘዉ መሰረት ሊወራረዱ እና ተመላሽ የሚሆን የመንግስት ገንዘብ ካለ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ተደርጎ ሪፖረት ሊቀርብ ይገባል፡፡ እንዲሁም ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ጥንቃቄ

ሊደረግና ማንኛዉም ክፍያ ሲፈፀም የመንግስት የክፍያ መመሪያዎች ተጠብቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

2.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- ሰራተኞች ለተቋማዊ ስልጠና በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለመከታተል የቆዩ ሲሆን ለሰልጣኞቹ ለቆይታቸው ለሚያስፈልጋቸው የቁርስ፣ የምሳ፣ እራትና አልጋ በደንቡ መሰረት ታስቦ በስልጠናው ወቅት ከሚያርፉበት ቦታ ወደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሚመላለሱበት የትራንስፖርት ሰርቪስ ስለሌለ እና የጉዞ ቆይታ ከቡሌ ሆራ እስከ ጅማ ያለውን የመንገድ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለመሄጃ 3 ቀን ለመመለሻ 3 ቀን በድምሩ ለመንገድ ቆይታ የ6 ቀን ታሳቢ ተደርጎ የተከፈለ ሲሆን ለ15 ቀን የሄዱት 15+6=21 ቀን ሲሆን ለ30 ቀን ስልጠና የሄዱት 36 ቀን ቆይታ ይሆናል፡፡ ሌላው ካለው የገንዘብ የመግዛት አቅም ጋር በተያያዘ በታሳቢነት የተጨመረ ሲሆን በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት በታሳቢነት የተጨመረው ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን ተደርጓል የገቢ ደረሰኝ አያይዘናል፣ ሳይፈቀድ ለተባለው በወቅቱ ጉዞው እና ተከፈለው አበል የተፈቀደ መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃውን አያይዘናል፡፡
- ብር 7,554.00 የተፈቀደ ስለሆነ ስራውም ስለመሰራቱ በማወራረጃው ላይ ጉዞውን የፈቀደው አካል ያጸደቀው ስለሆነ የኸው ታውቆ በብልጫ የተከፈለው ብር 1,845.00 ብቻ ወደ መንግስት ካዝና የሚመለስ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- ሰራተኞች ወደ አዲስ አበባና ሃዋሳ ሲሄዱ በተለመደው አሰራር የመንገድ ላይ ቆይታቸው ሳይካተት በመሆኑና የተጠቀሰው ቀን ለስራ የቆዩበትን ብቻ የሚያመለክት በመሆኑ ከቡሌ ሆራ ሃዋሳ 1 ቀን ከሃዋሳ አዲስ አበባ 1 ቀን ለጉዞ 2 ቀን በተመሳሳዩ መመለሻ 2 ቀን ስለሚጠቀሙ 4 ቀን የጉዞ ሲሆን የኸው ታሳቢ በማድረግ ልዩነቱን ብር 7,128.00 ተመላሽ እንዲሆን ተደርጓል ኮፒ የገቢ ደረሰኞችን አያይዘንል፡፡

2.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ተመላሽ እንደተደረገ እና ኮፒ የገቢ ደረሰኞችን አያይዘናል ቢባልም የቀረበ ኮፒ የገቢ ደረሰኝ እንደሌለ መግለጽ እንወዳለን፡፡

2.2.1 ግኝት፣ ለተቋሙ ላልተሰራ ስራ ክፍያ ፈጽሞ መገኘት፣

የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ሃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 1.ሀ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የመስሪያ ቤታቸውን ስልጣንና ኃላፊነት በመወጣትና የፀደቀውን በጀት መሰረት በማድረግ ወጪዎችን በመፈፀም በኩል መስሪያ ቤታቸውን የመምራትና የመወከል ፕሮግራሞችንና መስሪያ ቤታቸውን የሚመለከቱ ህጎች በማስፈጸም በኩል ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በቀን 30/05/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0859905 በምስራቅ ጉጂ ዞን ሊበን ወረዳ ቡራ ደራ ቀበሌ የአካባቢ ጥበቃ ስራ ለሰሩ ለ144 ሰዎች ለእያንዳንዳቸው የ15 ቀን በቀን ብር 50 ክፍያ እንዲከፈላቸው በማለት በድምሩ ብር 108,000.00 ለተቋሙ ላልተሰራ ስራ ከመንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ውጭ ለዩኒቨርስቲው ከተበጀተለት በጀት ላይ የተከፈላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.2.2 ስጋት፣

የክፍያ መመሪያን በመጣስ የሚከፈሉ ክፍያዎች የመንግስትን ገንዘብ ለጥፋት ይዳርጋል፡፡ እንዲሁም ለብልሹ አሰራሮች በር ሊከፍት ይችላል፡፡

2.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርስቲው ማናቸውንም ክፍያዎች ሲከፍል የመንግስትን የክፍያ አዋጆች፣ መመሪያዎች እና ደንቦች ተግባራዊ በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡ እንዲሁም ክፍያ ከመከፈሉ በፊት ዩኒቨርስቲው አገልግሎት ስለማግኘቱ ማረጋገጥ ይገባል ፡፡

2.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ስራው የተሰራው ለተቋሙ ነው ማለትም ከዩኒቨርሲቲው ዓላማ አንዱ የሆነው የማህበረሰብ አገልግሎት ስራ ሲሆን በዚህም የአካባቢ ጥበቃ ስራ መስራት የተራቆቱ አከባቢዎችን በጥቂት ወጪ እንዲያገግሙ ማድረግ ዋነኛ እና ተጠቃሽ ግብ ሲሆን በግኝቱ በተገለጸው በጉጂ ዞን በሊበን ወረዳ በዳራ ቀበሌ ውስጥ የአካባቢ ጥበቃ ለሚሰራው የተራቆቱ አከባቢዎች እንዲያገግሙ የሚሰራ በእቅድ የተያዘ ሲሆን በስራው ለተሳተፉ የማህበረሰብ ክፍሎች በቀን ሂሳብ 50 ብር ታስቦ

የተከፈለ ሲሆን ስራውም በዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት እቅድ ውስጥ ያለ እና ስራውም የተሰራው በእቅዱ መሰረት መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት እቅድ ውስጥ ያለ እና ስራውም የተሰራው በእቅዱ መሰረት መሆኑን እንገልጻለን ለተባለው ስራው በዩኒቨርሲቲው እቅድ ውስጥ ካለ ለምን በጀት አልተያዘለትም? ስለዚህ የተሰጠው መልስ ሲታይ ተቀባይነት የለውም፡፡

2.3.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ያለበጀት ዓመቱ የተከፈለ ክፍያ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 መሠረት የበጀት ዓመት ከሐምሌ1----ሰኔ 30 መሆኑን ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፦

- ብር 132,000.00 ለቢቅልቱ 1ኛ ደረጃ የህዝብ ማመላለሻ ማህበር በ2008 በጀት ዓመት የትራንስፖርት አገልግሎት ለሰጡበት ክፍያ፣
- ብር 216,725.46 ለአብዲሳ ኢሳ የማገዶ እንጨት ስራ ማህበር በሰኔ ውር 2008 ዓ/ም የማገዶ እንጨት ያቀረቡበት ክፍያ፣
- ብር 515,828.73 ለዲኤ አስመጪ ኃ.የተ.የግ.ማህበር የላብራቶሪ እቃዎችና ኬሚካሎችን በግንቦትና ሰኔ ወር 2008 ዓ.ም ስላቀረቡ ክፍያ፣
- ብር 420,756.07 ለዩኒቨርስቲው አስተዳደር ሰራተኞች የሰኔ ወር 2008 ዓ.ም የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣
- ብር 99,000.00 ለ3B የችግኝ አቅርቦትና መንከባከብ ማህበር በ2008 በጀት ዓመት ችግኝ ያቀረቡበት ክፍያ፣
- ብር 59,151.60 ለቡሌ ሆራ ሆቴል ለተማሪዎች በሰኔ ወር 2008 ዓ.ም ዳቦ ያቀረቡበት ክፍያ፣

በድምሩ ብር **1,443,461.26** የዕቃ ግዥን እና የአገልግሎት ክፍያን በበጀት ዓመቱ መክፈል ሲገባው ለዩኒቨርሲቲው ከተበጀተለት የ2009 በጀት ዓመት ላይ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.3.2 ስጋት፣

- የመንግስትን በጀት ከደንብና መመሪያ ውጪ መጠቀም የመንግስት መመሪያን ከመጣሱም በላይ የሒሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የበጀት ዓመቱን ወጪዎች እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- እንዲሁም በ2009 በጀት ዓመት ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎችን ሊያስተጓጉል ይችላል፡፡

2.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከመንግስት መመሪያና ደንብ ውጭ የሚከፈሉ ማናቸውም ክፍያዎች ተቀባይነት የሌላቸው በመሆኑ የበጀት ዓመቱን ግዢ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ እና በወጪ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.3.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመርያ ቁጥር 3/2003 መሰረት ድርጅቶች የበጀት አመቱ ገንዘብ መጠየቅያ ግዜ ካለፈ ቡኃላ እቃውን ገቢ ስለሚያደርጉ እና በዛን ወቅት የበጀት አመቱ ማጠናቀቂያ ስለሆነ የገንዘብ ጥያቄ አዘጋጅቶ ክፍያውን መፈጸም አስቸጋሪ ስለሚሆን ወደ ቀጣይ በጀት አመት ተሸጋግሯል፡፡ በቀጣይም ተደጋጋሚ ስህተት እንዳይፈጠር አገልግሎቱን የሚፈልገው አካል ከበጀት አመቱ መጨረሻ ወር አስቀድሞ ስራዎችን እንዲጠናቀቁ ይሰራል፡፡

2.4.1 ግኝት፣ የአበል መጠየቂያ ሳይቀርብ፣ ያለማስረጃ እና ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ፣

የመንግስት ሰራተኞች የቀን ዉሎ አበል መመሪያ ሰኔ /2004 ዓ.ም ክፍል 2 የዉሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 ማንኛዉም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታዉ ዉጭ ወደ ሌላ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ እለቱን መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ፤ ምሳና እራት በተመገበባቸዉ የክልላዊ ከተማ፣ የዞን ከተማ፣ የወረዳ ከተማና የከተማ አስተዳደሮች እንዲከፈል የተመደበዉን አበል ለእያንዳንዱ ቀን ይከፈላል፡፡ በተጨማሪም ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ ከሙሉ የአንድ ቀን ተመን ዉስጥ 10% ለቁርስ፣ 25% ለምሳ፣ 25% ለእራት እና 40% ለአልጋ የተመደበ መሆኑ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በዚሁ መመሪያ ክፍል 3 አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ማንኛዉም

የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ውጭ ወደ ሌላ ቦታ ለስራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የዉሎ አበል መጠየቂያ፣ መፍቀጃና መክፈያ ቅፆች ለጉዳዩ አግባብ ባላቸዉ ሰራተኞች ወይም ሃላፊዎች መሞላት እንዳለባቸዉ ይገልፃል፡፡ በተጨሪም በዚሁ አንቀፅ ላይ ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 የዉሎ አበል ተከፍሎት ወደ ሌላ የስራ ቦታ የተላከ ሰራተኛ ሲመለስ የቀን ዉሎ አበል ክፊያ መቆጣጠሪያና የስራ ክንዉን መመዝገቢያ ቅፅ በመሙላት የስራ መግለጫ ያቀርባል፡፡ እንዲሁም የውሎ አበል እንዲከፈለዉ የጠየቀዉ የስራ ሃላፊ በሰራተኛዉ የተሞላዉ ቅፅ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ እንዳለበት በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲዉ ከላይ ከተጠቀሰው መመሪያ ውጭ በተለያዩ ጊዜዎች አበል ሲከፍል፣

- አበል መጠየቂያ፣ መፍቀጃ እና መክፋያ ሳያስሞላ የዉሎ አበል ቅድሚያ መጠየቂያ ፎርም በሚል በፔሮል ብቻ በመክፈል እና ማወራረጃው ላይም በትክክል ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራት እና ለአልጋ የተመደበዉ ሳይሞላ ዝም ብሎ በጥቅሉ ከፍተኛ አበል በሚያስከፍሉ ቦታዎች ብቻ የተመደበዉን ቀን ብዛት በማሰብ በዘጠኝ የወጪ ቫውቸሮች በድምሩ ብር 222,383.00 ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣ ዝርዝሩን አባሪ 5 ላይ ይመልከቱ፡፡
- ከንብረት አስተዳደር ቡደን መሪ ለ9 የወንዶ ገነት ተፈጥሮ ደን ኮሌጅ ሰራተኞች ጠረጴዛ ስለገጣጠሙ የ49 ቀን አበል እንዲከፈላቸዉ በቀረበለት ጥያቄ መሰረት በቀን 30/01/09 በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0857839 ብር 54,243.00 ሲከፍል ዉል ስለመኖሩ ምንም ዓይነት ማስረጃ ሳይቀርብለት ክፍያ መፈፀሙን፣
- በቀን 30/11/08 በሳጥን ወጭ ማስመሰከሪያ ቁጥር 0867707 አበል ሲከፍል አበል የጠየቀም የፈቀደም አካል ሳይኖር፤ የተከፈላቸዉ ሰዎች ከየት እንደመጡ፤ እነማን እንደሆኑ የሚገልፅ ማስረጃ ሳይቀርብ የ2008 ዓ.ም የምርቃት በዓል የአበል መክፈያ ፎርም በሚል ብቻ በድምሩ ብር 56,519.00 ከመመሪያ ዉጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

በድምሩ ብር 333,145.00 የአበል መጠየቂያ ሳይቀርብ፣ ያለማስረጃ እና ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ አበል መሆኑን ታውቋል፡፡

2.4.2 ስጋት፣

- መንግስት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡
- የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- ከህግ እና መመሪያ ውጭ በመወሰን የሚከፈል ክፍያ ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡

2.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የተወራረዱ በሚል የተያዙ ወይም የታለፉ ሂሳቦች በድጋሚ ህጉ እና መመሪያዉ በሚለዉ እና በሚያዝዘዉ መሰረት ሊወራረዱ እና ተመላሽ የሚሆን በተጨማሪም ያለአግባብ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ተደርጎ ሪፖረት ሊቀርብ ይገባል ፡፡ እንዲሁም ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ጥንቃቄ ሊደረግና ማንኛዉም ክፍያ ሲፈፀም የመንግስት የክፍያ መመሪያዎች ተጠብቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

2.4.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- በደንቡም እንደሚታወቀው አዲሱ የአበል አከፋፈል በቦታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ አንድ ሰው ወደ አዲስ አበባ ወይንም ወደ ሌላ ቦታ ለስራ በሚቆዩበት ጊዜ በተለይም ረጅም ጉዞ ሲሆን ቁርስ፤ ምሳ፤ እራት የሚበሉበት እና የሚያድሩበት ቦታ ሰፊ ልዩነት ስለሚኖረው አንዳንድ ጊዜ የተወሰኑትን ታሳቢ አድርጎ መስራት ይታያል፡፡ ሆኖም ግን ፎርሙ ከተጠቀሰው ውስንነት ውጪ በአግባቡ የሚሞላ እና ከሰነዱ ጋር የሚያያዝ መሆኑ፤ እንዲሁም አንዳንድ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ከአንድ ከተማ ሴንተር አድርገው በመንቀሳቀስ የሚሰሩ በመሆናቸው እና የተለያዩ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ስለሚንቀሳቀሱ እና የሚፈልጉትን የምግብ እና የመኝታ አገልግሎት ቅርበት ወደ አለው ከተማ በመሄድ ስለሚያገኙ በስራው ወጣ ገብነት ጉድለቶች ያሉ ቢሆንም በቀጣዩ በፎርሙ መሰረት አጠናክረን እንሰራለን፡፡
- የወንዶ ገነት ደን ኮሌጅ ሰራተኞችን በተመለከተ በወቅቱ ዩኒቨርሲቲው ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች ለመግዛት ከወንዶ ገነት ደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ ዩኒቨርሲቲው ውል የገባ ቢሆንም እቃዎች ከወንዶ ገነት ተገጣጥመው ወደ ቡሌ ሆራ ሲጓጓዙ የአንድ

መኪና የመጫን አቅም በጣም ትንሽ ስለሆነ እና በመጓጓዝ እያለ እቃዎቹ እየተሰበሩ በመሆናቸው የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን በጠየቀው መሰረት እቃዎቹን መጥተው በግቢያችን እንዲገጥሙ በተደረሰው ስምምነት መሰረት ሲሆን በወቅቱ የተጻፈውን ደብዳቤ ስራው የተጀመረው በ2005-2006 በጀት ዓመት በመሆኑ ቀድሞ ከነበረው ሰነድ ጋር ያለ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ሰራተኞቹ እዚህ መጥተው እንዲሰሩ የተደረገው በዩኒቨርሲቲው ጥያቄ መሆኑን እንገልጻል ደብዳቤውን አያይዘናል፡፡

- ሌላው የአበል ክፍያ የተከፈለው በደንቡ እና በመመሪያው መሰረት ሲሆን ግለሰቦቹም የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች አይደሉም ነገር ግን ለ2009 የተማሪዎች ምረቃ በዓል በዩኒቨርሲቲው በደብዳቤ ተጋብዘው የግለሰቡ የጥሪ ደብዳቤ ለዳይሬክቶራችን ሲደርስ በወቅቱ በማናጅመንቱ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት እንግዶቹ የሚመጡበትን የቦታ ርቀት መሰረት ባደረገ ሁኔታ በሪጅስትረር ጽ/ቤት ጠያቂነት ክፍያው ሊፈጸም ችሏል፡፡ በመሆኑም ጥሪው በግለሰቦቹ ፍላጎት ሳይሆን በዩኒቨርሲቲው ስለሆነ ከግለሰቦቹ ተመላሽ የሚደረግ ገንዘብ አይኖርም፡፡

2.5.1 ግኝት፣ የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ የተገኘ፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16.26 ውል መፈረም ንዑስ አንቀጽ 16.27.4 በንዑስ አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሰረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ገደብ ውስጥ ዕቃውን ባያስረክብ (ሀ) አቅራቢ ሳይፈፅም በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 0.001% ወይም 1/1000 የጉዳት ካሳ መክፈል እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ድርጅቶች ውል አስሮ ግዥ ሲፈጽም በተዋዋሉበት ጊዜ ባለማቅረባቸው በድምሩ ብር **3,444,690.21** የጉዳት ካሳ ቀንሶ ማስከፈል ሲገባው ሙሉ ክፍያ የከፈለ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ 20 ዝርዝሩን እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- በቀን 23/02/09 በወጪ መስመስከሪያ ቁጥር 737669 ብር 348,797.29 ለቶፊቅ ሀቢብ የኮንስትራክሽንና የግብርና መገልገያ መሳሪያዎች ጅምላ ንግድ ለግንባታ እቃዎች ግዥ የተከፈለ ሲሆን በተገባዉ ዉል መሰረት

እስከ መስከረም 18/2009 ድረስ ማስገባት ሲገባው ንብረቱን በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ቁጥር 145031,145032 እና 145033 ገቢ የተደረገው በጥቅምት 18/2009 በመሆኑ ማስገባት ሲገባው ላዘገየበት 30 ቀን 348,797.29 *1/1000*30 =10,463.92 የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ሙሉ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣

- በቀን 30/12/08 በወጪ መስመስከሪያ ቁጥር 743420 ብር 3,128,000.00 ከኢምፔሪያል አይ ሲቲ ሶሉሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የኮምፒዩተር ግዥ በተገባዉ ዉል መሰረት እስከ ሀምሌ 30/2008 ድረስ ማስገባት ሲገባው ንብረቱን በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ቁጥር 204329 ገቢ የተደረገው ነሀሴ 26/2008 በመሆኑ ማስገባት ሲገባው ላዘገየበት 26 ቀን 3,128,000.00 *1/1000*26=81,328.00 የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ሙሉ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- በቀን 30/08/09 በወጪ መስመስከሪያ ቁጥር 0783722 ብር 276,000.00 ከአለምሰገድ ዓለሙ የእቃ ማመላለሻ ጋሪ ግዥ በተገባዉ ዉል መሰረት እስከ ጥር 25/2009 ድረስ ማስገባት ሲገባው ንብረቱን በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ቁጥር 144470 ገቢ የተደረገው የካቲት 10/2009 በመሆኑ ማስገባት ሲገባው ላዘገየበት 15 ቀን 276,000.00*1/1000*26 = 4,140.00 የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ሙሉ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- በቀን 13/03/09 በወጪ መስመስከሪያ ቁጥር 736377 ብር 890,000.00 ከዲኤ ዲፖርት/ዳንኤል አስፋው/ ኤክስ ሬይ/X-Ray/ ግዥ በተገባዉ ዉል መሰረት እስከ ሀምሌ 30/2008 ድረስ ማስገባት ሲገባው ንብረቱን በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ቁጥር 205221 ገቢ የተደረገው ህዳር 12/2009 በመሆኑ ማስገባት ሲገባው ላዘገየበት 107 ቀን 890,000.00*1/1000*107=95,230.00 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 890,000.00*10% = 89,000.00 የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ሙሉ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣

- በቀን 16/08/09 በወጪ መስመስከሪያ ቁጥር 386876 ብር 2,384,994.00 ከአስኮም ኢንዳስትሪያል ኃ/የተ/የግ/ማህበር የአይ ሲቲ እቃዎች ግዢ በተገባዉ ዉል መሰረት እስከ ታህሳስ 10/2009 ድረስ ማስገባት ሲገባው ንብረቱን በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ቁጥር 144313 ገቢ የተደረገው በጥር 22/2009 በመሆኑ ማስገባት ሲገባው ላዘገየበት 42 ቀን 2,384,994.00*1/1000*22=52,469.88 የጉዳት ካሳ መቀነስ ሲገባው አቅራቢው የይራዘምልኝ ጥያቄ ያቀረበበት ማስረጃ እና በዚሁ መሰረት የማናጅመንት ኮሚቴ የቀረበውን የይራዘምልኝ ጥያቄ አግባብነት በማየት ይሁንታውን የተቀበለበት የቃለ-ጉባዔ ማስረጃ ሳይኖር በግዥ ዳይሬክተሩ ብቻ በተጻፈ ደብዳቤ ሙሉ ክፍያ የተከፈለው መሆኑ፣
- በቀን 18/09/09 በወጪ መስመስከሪያ ቁጥር 748280 ብር በቀን 16/08/09 በወጪ መስመስከሪያ ቁጥር 386878 ብር 4,413,868.22 ከከነራ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የአይ ሲቲ እቃዎች ግዢ በተገባዉ ዉል መሰረት እስከ ታህሳስ 15/2009 ድረስ ማስገባት ሲገባው ንብረቱን በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ቁጥር 144314 እና 144366 ገቢ የተደረገው ጥር 22/2009 ሲሆን ድርጅቱ እቃዎቹን ለዩኒቨርሲቲው የጥራት ኮሚቴ ያስረከበው ጥር 10/2009 ስለሆነ ላዘገየበት 24 ቀን 4,413,868.22 *1/1000*24=105,932.83 የጉዳት ካሳ መክፈል ሲገባው ዩኒቨርሲቲው ብር 44,138.68 ብቻ እንዲከፍል በማድረጉ ልዩነቱ ብር 61,794.15 የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- ኢምፔሪያል አይ ሲቲ ሶሉውሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የአይ ሲቲ እቃዎች በብር 46,377,200.00 ግዢ በተገባዉ ዉል መሰረት እስከ ታህሳስ 19/2009 ድረስ ማስገባት ሲገባው የብር 20,113,500.00 ንብረት በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ቁጥር 144335 ገቢ የተደረገው ሚያዝያ 26/2009 በመሆኑ ላዘገየበት 126 ቀን

20,113,500.00*1/1000*126= 2,534,301.00 የጉዳት ካሳ መክፈል ሲገባው ዩኒቨርሲቲው የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱ፣

- ኢምፔሪያል አይ ሲቲ ሶሉውሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የአይ ሲቲ እቃዎች በብር 6,111,932.60 ግዢ በተገባዉ ዉል መሰረት እስከ ታህሳስ 19/2009 ድረስ ማስገባት ሲገባው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ቁጥር 149101 ገቢ የተደረገው ሰኔ 26/2009 በመሆኑ ላዘገየበት 187 ቀን 6,111,932.60 *1/1000*187= 1,142,931.40 ሲሆን የጉዳት ካሳው ከ10% መብለጥ ስለሌለበት 6,111,932.60 * 10%= ብር 611,193.26 የጉዳት ካሳ መክፈል ሲገባው ዩኒቨርሲቲው የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱ፣

2.5.2 ስጋት፣

አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት ዕቃውን ገቢ እንዲያደርጉ ካልተደረገ ዩኒቨርሲቲው ከገዛው ዕቃ ሊያገኝ ያቀደውን አገልግሎት እንዲያጣ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህም በስራ አፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

2.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው አቅራቢው (ድርጅቱ) የጉዳት ካሳውን እንዲከፍል በማድረግ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ካላቀረቡ የጉዳት ካሳ እንዲከፍሉ ማድረግ ወይም ያስያዙት ሲፒኦ ሊወርስ ይገባል፡፡

2.5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ድርጅቶች ውል በገቡበት ቀነ ገደብ መሰረት ለማቅረብ በዶላር እጥረት መቸገራቸውን በገለጹት እና በጠየቁት መሰረት ውል ማራዘሚያ ጊዜ የተራዘመላቸው በመሆኑና እቃውም በዩኒቨርሲቲው ግምጃ ቤት ከገባ በኃላ ጥራቱ እስኪረጋገጥና እና ሙሉ ርክክብ እስከሚደረግ ድረስ እስከ 10 ቀን እና ከዚያም በላይ የሚቆዩበት ሁኔታዎች ስለአሉ እና በአቅራቢው ባልሆነ ችግር ወደ ቅጣት ማስገበት ተገቢ ስለልሆነ በቀጣይ የአሰራር ማሻሻያዎችን በማድረግ በውል ግዢያቸው እንዲጠናቀቁ እናደርጋለን በወቅቱ የተደረገውን የግዜ ማራዘሚያ በማስረጃነት አቅርበናል፡፡

2.5.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በወቅቱ የተደረገውን የግዜ ማራዘሚያ በማስረጃነት አቅርበናል ቢባልም የግዜ ማራዘሚያ ማስረጃ በወቅቱ እንዳልቀረበልን መግለጽ እንወዳለን፡፡

2.6.1 ግኝት፣ ያለሂሳብ መደቡ የተመዘገበ፣

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 ቁጥር 3 የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች በየመደባቸዉ ተለይተዉ መመዝገብ እንዳለባቸዉ ይገልፃል፡፡ ነገር ግን ዩኒቨርሲቲዉ አንዳንድ ወጭዎችን በሚመዘግብበት ጊዜ ከተቀመጠላቸዉ የሂሳብ መደብ ውጭ በድምሩ ብር **10,165,685.61** መዝግቦ የተገኘ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከተመዘገበው ሂሳብ ውስጥ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ በ6233/ለመስተንግዶ/ ተመዝግቦ ቢሆን ኖሮ ብር 264,893.84 ከበጀት በላይ መጠቀሙን እና በትክክለኛው የሂሳብ መደብ በ6216 /ለምግብ/ ተመዝግቦ ቢሆን ኖሮ በብር 1,044,536.12 ከበጀት በላይ መሆኑን የሚያመላክት ከመሆኑም በተጨማሪ የወጪው ሂሳብም በተማሪዎች የወጪ መጋራት ላይም የማይታይ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩን አባሪ 6 ላይ ይመልከቱ

2.6.2 ስጋት፣

የመንግስትን በጀት ከደንብና መመሪያ ውጪ መጠቀም የመንግስት መመሪያን ከመጣሱም በላይ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሊሰሩ የታቀዱ መደበኛ ስራዎችን ሊያስተጓጉል ይችላል፡፡ ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የዩኒቨርሲቲውን የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ከማድረጉም በተጨማሪም የሂሳብ አያያዙም የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም መንግስት በተማሪዎች የወጪ መጋራት ላይም ያወጣውን ወጪ እንዳይሰበስብ ሊያደርገው ይችላል፡፡

2.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የወጪዎች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክክለኛ የወጪ ሂሳብ መደባቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ጥንቃቄ ሊደረግና

ማንኛውም ክፍያ ሲፈፀም የመንግስት የክፍያ መመሪያዎች ተጠብቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

2.6.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የተማሪዎች የፊልድ ጉዞን በተመለከተ የተሰጠው እና ፕሮፖዛሉ የቀረበው በተጨማሪ ስልጠና በመሆኑ በ6271 ወጪ መደብ እንዲያዝ ተደርጓል፡፡ የቀን ሰራተኛ ክፍያ በ6231 የተባለው ስራው የተሰራው በገጠር ቀበሌ ስለሆነ እና በ50 ብር ተባዝቶ የተከፈለ መሆኑ ፣ የመኪና ኪራይ ለትራንስፖርት ብለን የተከራየን በመሆኑ፣ የአገልግሎት ክፍያ በ6256 ለአልጋና ለተለያዩ አገልግሎቶች የተከፈለ መሆኑ፣ የሞተር ኪራይን እና የስልክ አገልግሎትን በተመለከተ በቀጣዩ ስህተቱ እንዳይደገም እንሰራለን፡፡ ሌሎች የአሰራር ችግሮችን የሰራተኛውን ብቃት በስልጠና በማጎልበት የምንሰራበት መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.7.1 ግኝት፣ የወጪ ማስረጃ የሌለው ክፍያ፣

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001፣ በፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 እና በፌዴራል መንግስት የሂሳብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለማንኛውም ወጪ ክፍያ መፈጸም የሚገባው ተመጣጣኝ የክፍያ ደረሰኝ በማስረጃነት ሲቀርብ ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲው በድምሩ ብር **576,042.45** የወጪ ደረሰኝ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.	ቀን	የባንክ ወጪ ማስመስያ ቁጥር	የድርጅት ስም	የወጪው ምክንያት	የተከፈለው የገንዘብ ልክ
1	08/06/09	388819	አዳማሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	የላባራቶሪ ክፍያ	346,416.80
2	30/10/09	388695	አዳማሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	የላባራቶሪና የአልጋ ክፍያ	209,625.65
3	11/02/09	742935	ለመንግስትዩኒቨርሲቲዎች የምክክር መድረክ	የአባልነት መዋጮ	20,000.00

ድምር	576,042.45

2.7.2 ስጋት፣

ዩኒቨርስቲው ለፈፀመው ክፍያ ማስረጃ ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል።

2.7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውንም ክፍያዎች ከመክፈሉ በፊት ማስረጃ/ማወራረጃ /ሊሆኑ የሚችሉ ህጋዊ ደረሰኞችን ክፍያው ከተፈፀመላቸው አካሎች በመቀበል ከክፍያ ሰነዱ ጋር መያያዙን በማረጋገጥ ከፍያ ሊከፈል ስለሚገባ ከሚመለከተው አካል ማስረጃውን በማስመጣት ከወጪው ሰነድ ጋር ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

2.7.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የላብራቶሪ ክፍያዎች በወቅቱ የትምህርት ግዜ እንዳይባክን ታስቦ የባንክ ስሊፕ ጉዞን በኃላፊነት ለሚመራው መምህር የገቢ ደረሰኝ ይዞ እንዲመጣ ቢደረግም በወቅቱ ባለማምጣቱ እና የሂሳብ ክፍልም በደራሽ ስራ በመጠመዱ ክትትል ሳይደረግ የቆየ ሲሆን ኦዲተሮቹ የመውጫ ስብሰባ ከማድረጋቸው በፊት ደረሰኙ እንዲቀርብ አድርገናል አሁንም ማስረጃ ኮፒውን አያይዘናል።

2.7.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

የመውጫ ስብሰባ ከመደረጉ በፊት እና ከዚያም በኂላ ደረሰኙ ሊቀርብ ይገባ ነበር። አሁንም ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል።

2.8.1 ግኝት፣ ከመመሪያ ውጭ የተፈጸመ የመኪና ጎማ ግዥ፣

የፌደራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀፅ 16.5 (ሠ) የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጭ ማመልከት (መጠቀስ) የለበትም ይላል። ነገር ግን ዩኒቨርሲቲዉ በቀን 30/03/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 744361 በብር 199,340.00፣ በቀን 30/05/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 766174 በብር 193,200.00 እና በቀን

05/07/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 765287 በብር 96,370.00 በድምሩ ብር 488,910.00 የመኪና ጎማ ግዥ በዋጋ የማቀረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈፅም የአንድ አምራች ድርጅትን የንግድ ስም በመጥቀስ ብሪጅስቶን ወይም ተመሳሳይ ጥራት ያለው በማለት ከላይ ከተጠቀሰው መመሪያ ውጭ ግዥ የፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.8.2 ስጋት፣

- በውድድር ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ሊያሣጣ ይችላል፡፡
- ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

2.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲዉ የተለያዩ ግዥዎችን ሲፈፀም መንግስት በየጊዜዉ በሚያወጣቸዉ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይከሰት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.8.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ሰኔ 2002 ዓ/ም የወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 2 አንቀጽ 6.5 /ሠ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ወቅት ፍላጎት በትክክል ሊገለጽ የሚችል መግለጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ግዥው ለተለየ ፕላንት ወይም መስሪያ የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎች የሚመለከት ሲሆን የአምራቹን ስም በመጥቀስ ወይም ተመሳሳይ በሚል ሃረግ እንዲተከል መመሪያው ይፈቅዳል ይህንም መሰረት በማድረግ ጎማ ጥርስ ያለው መሬትን ቆንጥጦ መያዝ የሚችል የማይንሸራተት በሚለው ብቻ የጎማውን ጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ እና ለመገምገም አስቸጋሪ በመሆኑ ተመሳሳይ የሚለውን ቃል ለመጠቀም ችለናል፡፡

2.8.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

መመሪያውን ተጠቅሶ ዩኒቨርሲቲው የሰጠው መልስ ተቀባይነት የለውም ምክንያቱም መመሪያው ራሱ ይዘቱ በትክክል አልተጠቀሰም እና የሚለውየቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጭ ማመልከት (መጠቀስ) የለበትም ይላል፡፡“ ዩኒቨርሲቲው ግን ከአንድ የምራች ድርጅትን

የንግድ ስም በመጥቀስ ብሪጅስቶን ወይም ተመሳሳይ ጥራት ያለው በማለት መጥቀሱ አንባብነት የለውም ስለሆነም በመመሪያው መሰረት ግዢው መፈጸም አለበት፡፡

2.9.1 ግኝት፣ ከማዕቀፍ ግዥ ውጭ የተፈጸመ፣

የፌደራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ክፍል 6 አንቀፅ 27.2 ላይ በሁሉም ወይም በተወሰኑ መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለግ እቃና አገልግሎት ግዥ የሚፈፀመዉ የማዕቀፍ ስምምነትን መሰረት በማድረግ ግዥ መፈፀም እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሰረት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 184/2002 በተሰጠዉ ተግባርና ሃላፊነት መሰረት የፌደራል ባለበጀት የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸዉን ተመሳሳይ ዕቃዎች በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ለመፈፀም ዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ አዉጥቶ አሸናፊ ተጫራቾችን በመለየት ከ2008-2010 ዓ.ም ለሶስት ዓመታት የሚቆይ ኮምፒዩተሮችን፤ የተሽከርካሪ ጎማዎችን እና ሌሎችንም የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ኮንትራት ከአንድ አቅራቢ ጋር ዉል በመፈራረም ከተመረጠዉ ድርጅት የግዥ ትዕዛዝ በመስጠት ግዥ እንዲፈፀም ከመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መ/ቤት ለቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ በቀን 08/09/08 በደብዳቤ ቁጥር ግንማ1/4/1054/2078 በተፃፈ ደብዳቤ ትዕዛዝ የተላለፈ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ዩኒቨርሲቲው፡-

- በቀን 30/03/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 744361 በብር 199,340.00፣ በቀን 30/05/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 766174 በብር 193,200.00 እና በቀን 05/07/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 765287 በብር 96,370.00 በድምሩ ብር **482,910.00** የመኪና ጎማ ግዥ በማዕቀፍ ግዥ በተቀመጠዉ አቅጣጫ እና ድርጅት መገዛት ሲገባዉ ዩኒቨርሲቲዉ በራሱ ጊዜ ከላይ ከተጠቀሰዉ መመሪያና ትዕዛዝ ውጭ በዋጋ የማቅረቢያ የግዥ ዘዴ /በፕሮፎርማ/ ግዥ የተፈጸመ መሆኑን፣
- የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አንዱን ሌኖቭ ኮር i7 ላፕ ቶፕ ኮምፒዩተር ከነቫት በብር 17,316.00 ከብሪጅ ቴክ ኃ/የተ/የግ/ማ ግዥ እንዲፈጸም ያሳወቀ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በራሱ ጨረታ በማውጣት በቀን

30/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 743420 አንዱን ሌኖቭ ኮር i7 ላፕ ቶፕ ኮምፒዩተር ከነቫት በብር 62,560.00 ከኢምፔሪያል አይ ሲቲ ሶሉሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ግዥ የፈጸመ በመሆኑ የተገዛው ኮምፒዩተር ብዛት 50 ሲሆን 62,560.00*50= ብር 3,128,000.00 ክፍያ ፈጽሟል። በመሆኑም በመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መሰረት ቢገዛ 17,316.00*50= ብር 865,800.00 ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በራሱ ጨረታ በማውጣት የገዛው በብር 3,128,000.00 በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በተዋዋለው በማዕቀፍ ስምምነት ውል መሰረት ባለመግዛቱ 3,128,000.00-865,800.00= ብር 2,262,200.00 የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ በብልጫ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

- የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አንዱን ዴል ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር ከነቫት በብር 11,633.40 ከአልታ ኮምፒዩተር ኃ/የተ/የግ/ማ ግዥ እንዲፈጸም ያሳወቀ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በራሱ ጨረታ በማውጣት በቀን 28/01/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 743429 አንዱን ዴል ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር ከነቫት በብር 39,479.34 ከኳሊቲ ኮምፒዩተርስ አክሰሰሪስ ግዥ የፈጸመ በመሆኑ የተገዛው ኮምፒዩተር ብዛት 200 ሲሆን 39,479.34*200= ብር 7,895,868.00 ክፍያ ፈጽሟል። በመሆኑም በመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መሰረት ቢገዛ 11,633.40*200= 2,326,680.00 ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በራሱ ጨረታ በማውጣት የገዛው በብር 7,895,868.00 በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በተዋዋለው በማዕቀፍ ስምምነት ውል መሰረት ባለመግዛቱ 7,895,868.00-2,326,680.00= ብር 5,569,188.00 የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ በብልጫ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡
- የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አንዱን ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር ኮር i7 ከነቫት በብር 17,958.40 ከአሙሉቴክ ኃ/የተ/የግ/ማ ግዥ እንዲፈጸም ያሳወቀ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በራሱ ጨረታ በማውጣት በቀን

28/01/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 743431 አንዱን ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር ኮር i7 ከነቫት በብር 54,050.00 ከራኪን ኢንፖርተር ግዥ የፈጸመ በመሆኑ የተገዛው ኮምፒዩተር ብዛት 120 ሲሆን 54,050.00*120= ብር 6,486,000.00 ክፍያ ፈጽሟል።በመሆኑም በመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መሰረት ቢገዛ 17,958.40*120= 2,155,008.00 ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በራሱ ጨረታ በማውጣት የገዛው በብር 6,486,000.00 በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በተዋዋለው በማዕቀፍ ስምምነት ውል መሰረት ባለመግዛቱ 6,486,000.00 - 2,155,008.00 = ብር 4,330,992.00 የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ በብልጫ እንዲወጣ ተደርጓል።

ዩኒቨርሲቲው የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በተዋዋለው በማዕቀፍ ስምምነት ውል መሰረት ኮምፒዩተሮችን ባለመግዛቱ በድምሩ ብር 12,162,380.00 የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ በብልጫ እንዲወጣ መደረጉ ታውቃል፡፡

2.9.2 ስጋት፣

በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም አያስገኝም፡፡ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ የመንግሥትም ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡ የግዥ መመሪያ ተግባራዊ ባለመደረጉ ዩኒቨርሲቲው ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

2.9.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በአሰራጨው የጋራ መጠቀሚያ እቃዎች ለፌደራል መንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች አቅርቦቱን ሲፈልጉ በማዕቀፍ ስምምነት ውል መሰረት መግዛት እየተቻለ አለማድረጉ አግባብ ባለመሆኑ ለምን ግዢው አገልግሎቱ ከሰጠው የግዢ ትእዛዝ ውጭ ሊፈጸም እንደቻለ ሪፖርት እንዲቀርብ ሆኖ ለወደፊቱ ማንኛውም በማዕቀፍ የሚፈጸም ግዥ በትእዛዙና በመመሪያው መሠረት ለመፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ኃላፊነቱን በመወጣት የመንግሥትን ውስን ሃብት በቁጠባ ለመጠቀም አስፈላጊውን ሁሉ ሊፈጽም ይገባል፡፡

2.10.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የፌደራል ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ/ም ክፍል 6 አንቀጽ 27.11(ሀ) ላይ እንደተገለጸው የግዥ ትእዛዝ የሚሰጡት የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ለሚፈጽመው አካል የግልጸትና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ግዥው በማዕቀፍ ስምምነት የተፈጸመ መሆኑን መረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ስለዚህ ዩኒቨርሲቲው ግዥውን የፈጸመው በማዕቀፍ ስምምነት ላይ ያለው ለምንፈልገው አገልግሎት አለመሆኑ ከተረጋገጠ በኂላ እንዲሁም በ2008 ከማእቀፍ ግዢ የገባ ጎማ ጥራቱን የጠበቀ ጎማ ባለመሆኑ ያለ አገልግሎት በንብረት ክፍል ተከማችቶ የሚገኝ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው እንዲገዛ ተደርጓል፡፡ የተገዙት ኮምፒዩተሮችም በአይነታቸውና በስፔስፊኬሽን ቴክኒክ ብቃታቸው የተለዩና ሰርቨሮችን ማንቀሳቀስ የሚችሉና የተለዩ በመሆናቸው ለአይ ሲቲ ዲፓርትመንት ተጠይቀው የተገዙና ከማእቀፍ ግዥ የተለዩ መሆናቸው እንዲታወቅ፣ በመሆኑም core i7 የሚለው ብቻ ዩኒቨርሲቲው የሚፈልገውን የቴክኒክ ብቃት የሚያሟላ ባለመሆኑ፣ system model ስለሚለያይ (የሚለዩበት ዋና ዋና መገለጫዎች→ board artcthecture, display graphics, hardware and software upgradability, dual boot for servers, specification difference, graphics memory, system memory, storage etc.) ዝርዝር ሁኔታዎች ታይተው ለተለየ አገልግሎት የተገዙ መሆንችውን እንገልጻለን፡፡

2.9.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

የተገዙት ኮምፒዩተሮችምና የመኪና ጎማ በአይነታቸውና በስፔስፊኬሽን ቴክኒክ ብቃታቸው የተለዩና ሰርቨሮችን ማንቀሳቀስ የሚችሉና የተለዩ በመሆናቸው ለአይ ሲቲ ዲፓርትመንት ተጠይቀው የተገዙና ከማእቀፍ ግዥ የተለዩ መሆናቸው እንዲታወቅ፣ ብሎ መልስ የሰጠው ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ማስፈቀድ ነበረነት እንጂ በራሱ መወሰን አልነበረበትም፡፡

2.10.1 ግኝት፣ የውል ቀነ ገደብ የሌለው ውልን በተመለከተ፣

በፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 አንቀፅ 16.7 የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 16.7.3 ለ የውል አፈፃፀም በሚለው ስር በውል ሰጪና

በውል ተቀባይ መካከል ውል ሲዋዋሉ ውል ተቀባዩ አቅርቦቱን የሚጀምርበትንና የሚያጠናቅቅበትን ግዜ መጠቀስ እንዳለበት በመመሪያው የተጠቀሰ ቢሆንም፣ ዩኒቨርስቲው ከኤቨር ሻይን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ጋር የላብራቶሪ ዕቃዎችንና ኬሚካሎችን በብር 1,095,950.00 ለመግዛት ውል የተዋዋለ ሲሆን በውሉ ላይ ውሉን የተፈራረሙበት ቀን እና አቅራቢው አቅርቦቱን የሚጀምርበትና የሚያጠናቅቅበት ቀን ሳይጠቀስ፣ በቀን 25/11/08 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 737725 ብር 309,049.74 የከፈለ ሲሆን የግዥው ውል መንግስት ካወጣው የግዥ አፈጻፀም መመሪያ ውጪ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.10.2 <u>ስጋት፣</u>

አቅራቢው ዕቃዎቹን የሚያስረክብበት የጊዜ ቀነገደብ ካልተጠቃሰ እቃዎቹን በሚፈለጉበት ጊዜ እንዳይቀርቡ ያደርጋል፣ ይህም ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎችን በወቅቱ እንዳይሰሩ ያደርጋል፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርስቲው ማግኘት ያለበትን የጉዳት ካሳ እንዳያገኝ ሊያደርግ ይችላል ፡፡

2.10.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ግዥዎች በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መከናወን አለባቸው። ለወደፊቱም መመሪያን የተከተለ ግዥ እንዲከናወን ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.10.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የውል ሰነድ በተለያየ ኮፒ ስለሚዘጋጅ በስህተት ለፋይናንስ የተሰጠው ኮፒ ላይ ሳይጻፍ ቀርቶ ሲሆን ሌሎች ሰነዶች ላይ ግን በደንብ ጊዜ ገደቡ ተገልጾዋል፡፡ የተፈጠረው ክፍተት ለወደፊት የሚስተካከል ይሆናል፡፡

2.11.1 <u>ግኝት፣</u> <u>የተማሪዎች የምግብ ግብዓት ርክክብን በተመለከተ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ በጀት የሚገዛው የተማሪዎች የምግብ ግብዓት እና እቃ በየቀኑ በተዘጋጀ የርክክብ ቅጽ ላይ በየቀኑ በትክክል ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን፣ ቆጥሮና አስመዝኖ በየእለቱ ተፈራርሞ ማስገባት ሲኖርባቸው በተወሰደው ናሙና

የብር 3,659,245.43 የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴው ሳይፈራረም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ በማድረግ ብቻ ለአቅራቢዎቹ ክፍያ እንደሚከፈላቸው በቀረበው የክፍያ ሰነድ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

2.11.2 <u>ስጋት፣</u>

በየቀኑ የሚገቡት የምግብ ግብዓቶች እና እቃዎች የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴዎች በሌሉበት በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ መደረጉ የምግብ ግብዓቶች እና እቃዎች ትክክለኛነትን ስለማያረጋግጥ ክፍያው ትክክለኛ ነው ለማለት ስለማያስደፍር ለሙስናና ለብልሹ አሰራር በር ከመክፈቱም በላይ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.11.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴዎች በተገኙበት በየቀኑ በተዘጋጀ የምግብ ግብዓት እና እቃ ርክክብ ቅጽ ላይ በየቀኑ በትክክል ጥራቱን የጠበቀ የተማሪዎች የምግብ ግብዓት እና እቃን ቆጥሮ አስመዝኖ በማረጋገጥ በየእለቱ ተፈራርሞ ማስገባት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች መንግስት ከፍተኛ ውጪ መድቦ የሚገዛው የምግብ ግብዓቶች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲደረግ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡

2.11.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ለግብዓቱ ርክክብ ኮሚቴ የተዋቀረ ሲሆን ለክትትልና እና ቁጥጥር የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ነው፡፡ ስለዚህ የተማሪዎች አገልግሎት በኩል እንደዚህ ዓይነት ክፍተት እንዳይፈጠር ለወደፊቱ እንዲታረም እናረጋለን፡፡

2.12.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በጥራት ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የገባ ንብረትን በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር ክፍል ሶስት የስቶክ አስተዳደር ስርዓት ስቶክን ስለመቀበል በሚለው ስር የእቃ ግምጃቤት ኃላፊው የዕቃውን ትክክለኛነት ከተሰጠው ትዕዛዝ የዕቃ ዝርዝር (specification) ጋር በማመሣከር ወይም ባለሙያ የሚፈልግ ከሆነም በባለሙያ ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ማግኘት እንዳለበት ይገልፃል ፡፡ ይሁን እንጂ ዕቃዎች ተገዝተው ሲመጡ ተጫራቾች ባሸነፉባቸውና ባቀረቡት ናሙና መሰረት መገዛታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ስናከናውን ለኦዲት ከተመረጡት

ውስጥ ከ6 ድርጅቶች ላፕ ቶፕ ኮምፒዩተር፣ የስፖርት ትጥቆች፣ የስቴሽነሪ እቃዎች፣ የውሃ ባልዲዎች፣ ስፖት ሪዲንግ ካርዶች እና የፕሪንተር ቶነሮች በናሙናው መሰረት ግዥው የተፈጸመ ለመሆኑ ከዕቃ ጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴዎች (ከባለሙያዎች) ስለትክክለኛነቱ ማስረጃ ሳይቀርብ የብር 4,359,605.44 ንብረት ክፍል ገቢ ተደርገው ክፍያ ለአቅራቢዎች የተፈጸመላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

2.12.2 ስጋት፣

በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተጠየቀው የግዥ ፍላጎት እና ለናሙና ከቀረበው ውጭ ግዢው ከተፈጸመ ጥቅም ላይ ካለመዋሉም በላይ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል።

2.12.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማንኛውም ግዥዎች በፌደራል መንግሥት የግዥ ህግ እንዲፈጸም ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ንብረቱ ገቢ ከመሆኑ በፊትና ክፍያው ከመፈጸሙ በፊት በስፔስፍኬሽኑ እና በናሙናው መሰረት ለመሆኑ በባለሙያ ወይም በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ተረጋግጦና ለመረጋገጡም ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.12.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ስለሆነ ባለሙያ በቦታው ድረስ በመላክ በቀረበው ናሙና መሆኑ ከተረጋገጠ በኃላ የተገዛ ነው ሆኖም ግን የኮሚቴ ቃለ ጉባኤዎች ከክፍያ ሰነድ ጋር እንዲዙ እናደርጋለን፡፡

2.13.1 ግኝት፣ ያለውድድር የቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ፣

የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ክፍል 4 አንቀጽ 15.4 መሰረት ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሰነድ መያዝ ይኖርበታል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- በብር 632,950.00 ከ3B ችግኝ አቅራቢና መንከባከብ ማህበር የችግኝ ግዥ ክፍያ፣
- በብር 2,248,969.74 ከተለያዩ 10 ድርጅቶች የተሽከርካሪ ጥገና እና ኪራይ አገልግሎት ግዥ፣
- ብር 127,800.00 ከአቶ ሚለዮን አበራ የተበላሹ የፋይበር መስመሮችን ለማስተካከል የአገልግሎት ግዢ፣
- ብር 608,321.19 ከቡሌ ሆራ ሆቴል በተለያዩ ቀናት የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ፣
- በብር 500.000.00 ለልጅ የንጉስ ጠቅላላ ንግድ ስራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የውሃ መቅጃ ባልዲ ስላቀረቡ በሚል ክፍያ የከፈለ ሲሆን ግዥው በግልፅ ጨረታ መግዛት ሲገባ በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ መሆኑ እና እንዲሁም አቅራቢው ሊያቀርብ የተዋዋለው ባለ 25 ሊትር ባልዲ አንዱን ባልዲ በተጋነነ ዋጋ በብር 1000.00 ሂሳብ ሲሆን ንብረት ክፍል በንብረት ገቢ ደረሰኝ ቁጥር 145973 ገቢ የሆነው ባለ 20 ሊትር የውሃ መቅጃ ባልዲ በዚሁ ዋጋ መሆኑ፣

በድምሩ የብር 4,118,040.93 ግዥ በቀጥታ አገልግሎቱን ከሚሰጠው ድርጅት ውል በመዋዋል ያለውድድር ወይም ከሚመለከተው አካል በልዩ ሁኔታ ሳያስፈቅድ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.13.2 ስጋት፣

- በውድድር ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ሊያሣጣ ይችላል፡፡
- በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥ ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት አይቻልም፡ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡
- የመንግሥትም ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.13.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ግዥ ሲያከናዉን የግዥ ደንብና መመሪያን ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ካልተቻለም ከሚመለከተው አካል አገልግሎቱን ለመግዛት ፈቃድ ማግኘት

አለበት፡፡ ለወደፊቱም መሰል ስህተቶች እንዳይከሰቱ የእርምት እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

2.13.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ባልዲውን በተመለከተ ግዢው በግልጽ ጫረታ የተፈጸመ ነው ሆኖም ናሙና እንዲገመገም ናሙና ገምጋሚ ኮሚቴ የተዋቀረ ሲሆን ከቀረቡት ናሙና ውስጥ ባለ 25 ሊትር ባለመኖሩ ለመምረጥ የተቸገሩ ሲሆን ነገር ግን የውሃ ባልዲው በተማሪዎች ምግብ ቤት አገልግሎት በጣም ስለሚፈለግ ከቀረቡት ናሙናዎች ውስጥ ባለ 15 እና 20 ሊትር ባልዲ ብቻ በመኖሩ እቃውን በጭራሽ ከምናጣ በማለት ለ25 ሊትር የሚቀርበውን እና ተመሳሳይ አገልግሎት መስጠት የሚችል ባለ 20 ሊትር ኮሚቴው የመረጠው ሲሆን በዛው መሰረት ድርጅቱ ለዩኒቨርሲቲው አቅርበዋል፡፡ የመስተንግዶ ግዥ ትእዛዙ የተሰጠው በግዥ ክፍል ባይሆንም ሆቴሎች ለማወዳደር ተመሳሳይ ደረጃ እና ጥራት ያላቸው ሆቴሎች ከተማችን ውስጥ ስለሌሉ ዩኒቨርሲቲው የወሰደው የግዥ ሁኔታ በሜኑ እንዲጠቀሙ ተደርጓል፡፡ የችግኝ ግዥም ከዚህ ቀደም ከሃዋሳ እና ከቢሾፍቱ በከፍተኛ ዋጋ ከሚገቡት ችግኞች ጋር ሰፊ የዋጋ ልዩነት በማነስ ያላቸው እና ግብአቱን ሌላ ተጨማሪ ተጓዳኝ ወጪዎችን ዩኒቨርሲቲው ሳያወጣ ጥቃቅን እና አነስተኛ ማህበራት በአከባቢያችን በመኖራቸው ለውድድር ያላቸውን አቅርቦት ዩኒቨርሲቲው ግቢውን አረንጓዴ ለማድረግ ብዛት ያለው ችግኝ በመፈለጉ እና ተወዳዳሪ ባለመኖሩ ያሉትን ትቃቅን እና አነስተኛ ችግኙን እንዲቀርቡ ተደርጓል ፤ የተሽከርካሪ ጥገናና ኪራይ ወደ ካምፓኒ በመላክ ስናሰራ የቆየን ሲሆን በ2009 ግልጽ ጫረታ አውጥተን ስምምነት አስረን አገልግሎቱን እያገኘን ሲሆን በግኝቱ የተገለጸው የጨረታ ሂደቱ እስከሚያልቅ እና አዳዲስ ተሽከራካሪዎች 10,000 ኪ.ሜ እስከሚሄዱ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰአት ሙሉ በሙሉ ቀጥታ ግዢ አቁመናል፡፡

2.14.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>የግዥ ማስታወቂያን በተመለከተ፣</u>

ከታህሳስ 01 ቀን 2008 ዓ/ም ጀምሮ ተሻሽሎ ተፈጻሚ በሆነው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ ቁጥር 6(5) መሰረት በአለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈጸሙትን ግዥዎች ጨምሮ ለግንባታ ስራ ብር 20,000,000.00 ለእቃ

ግዥ ብር 6,000,000.00 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ግዥዎች ሲፈጸሙ የጨረታ ማስታወቂያው በጋዜጣ በወጣበት ተመሳሳይ ጊዜ በኤጀንሲው የመረጃ መረብ (ድረ-ገጽ) ላይ ለህዝብ ይፋ መደረግ እንዳለበት ያዛል፤ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፣

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስ/ቁጥር	የግዢው ዓይነት	የድርጅቱ ስም	የገንዘቡ መጠን
1	22/05/09	748252	የአይ ሲቲ እቃዎች	ኢምፔሪያል አይ ሲቲ ሶሉሽን ኃ/የተ/የግ/ማ	26,263,700.00
2	28/01/09	743429	የኮምፒዩተር ግዥ	ኳሊቲ ኮምፒዩተርስ አክሰሰሪስ	7,895,867.80
3	28/01/09	743431	የኮምፒዩተር ግዥ	ራኪን ኢንፖርተር	6,486,000.00
				ድምር	**40,645,567.80**

ከላይ የተዘረዘረው ብር 40,645,567.80 ግምት ያላቸው እቃዎች ግዥ ሲፈጸም የግዢ ማስታወቂያውም ሆነ አሸናፊ አቅራቢ ድርጅቶችን በኤጀንሲው ዌብ ሳይት አማካኝነት ለህዝብ ይፋ እንዲሆን አለመደረጉ ታውቋል፡፡

2.14.2 ስጋት፣

የወጣው የመንግስት የግዢ መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡

2.14.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በመመሪያው መሰረት ለግንባታ ስራ ብር 20,000,000.00 ለእቃ ግዥ ብር 6,000,000.00 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ግዥዎች ሲፈጸሙ የጨረታ ማስታወቂያው በጋዜጣ በወጣበት ተመሳሳይ ጊዜ በኤጀንሲው የመረጃ መረብ (ድረ-ገጽ) ላይ ለህዝብ ይፋ መደረግ ይኖርበታል፡፡በመሆኑም ለወደፊቱም መመሪያው በሚያዘው መሰረት ግዥዎች ሲፈጸሙ ማስታወቂያውም ሆነ አሸናፊ አቅራቢ

ድርጅቶችን በኤጀንሲው ዌብ ሳይት አማካኝነት ለህዝብ ይፋ እንዲሆን ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

2.14.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በቀጣይ ተግባራዊ እናደርጋለን በአሁኑ ሰአትም አየር ላይ ያለ ጫረታ በዚህ ሂደት እንዲልፍ አድርገናል፡፡

2.15.1 <u>ግኝት፣</u> <u>የጉዳት ካሳ ያልተቀነሰ የግንባታ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ሰኔ/2002 ባወጣው የግዢ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 16 ንዑስ ቀጥር 25 መሠረት ከመንግሥት መ/ቤቱ ጋር ውል የገባው አቅራቢ በውሉ መሠረት አገልግሎቱን በወቅቱ ባለማቅረቡ በውሉ መጠን ላይ በየቀኑ 1/1ሺኛ የጉዳት ካሳ መክፈል እንደሚገባው እና የጉዳት ካሳው ከውሉ ዋጋ 10 በመቶ የሚበልጥ ሲሆን ውል የገባው የመንግስት መ/ቤት ውሉን መሰረዝ እንደሚችል ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው የግንባታ ሥራዎች በመመሪያው መሠረት ክትትል የሚደረግባቸውና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ በተለያዩ ተቋራጮች የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ከግንባታ ጽ/ቤቱ በተገኘ መረጃና ትንተና በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

- ማት ጠ/ሥ/ ተቋራጭ ሁለት ዶርሚታሪ ሁለት ሴሚናር ክፍል እና አንድ መመገቢያና ክችን ግንባታ በብር 158,769,061.59 እስከ ሰኔ 08/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 68% ላይ የሚገኙ ሲሆን 32% /158,769,061.59*32/100= 50,806,099.71/ የቀረው በመሆኑ እና በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ22 ቀናት በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 50,806,099.71 *22*1/1000=1,117,734.19 ገቢ አለመደረጉን፣

- ካሱ ገ/ጻዲቅ ጠ/ሥ/ተቋራጭ ሁለት ዶርሚተሪ እና የመዝናኛ ግንባታ በብር 108,056,974.44 በተገባ ውል እስከ ሰኔ 08/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 64% ላይ የሚገኙ ሲሆን 36% /108056974.44*36/100= 38,900,510.80/ የቀረው በመሆኑ እና በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ22 ቀናት በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 38,900,510.80 *22*1/1000=855,811.24 ገቢ አለመደረጉን፣

- ኤፍ ኢ ኮንስትራክሽን Administration Building A,B,C &E Front fence & main gate) ግንባታ በብር 102,625,949.57 በተገባ ውል እስከ ህዳር/10/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ የካቲት 13/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 77% ላይ የሚገኙ ሲሆን 23% /102,625,949.57*23/100=23,603,968.40 የቀረው በመሆኑ እና በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ135 ቀናት ወይም ከ4 ወር በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 23,603,968.40*135*1/1000=3,186,535.73 ገቢ አለመደረጉን፣

- ኤፍ ኢ ኮንስትራክሽን Dormitory E&H Dinning Hall,Kitchen & Store ግንባታ በብር 155,468,196.41 በተገባ ውል እስከ ሰኔ 30/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 12/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 66% ላይ የሚገኙ ሲሆን 34% /155,468,196.41*34= 52,859,186.80 የቀረው በመሆኑ እና መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ22 ቀን በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 52,859,186.80 *22*1/1000=1,162,902.11 ገቢ አለመደረጉን፣

- ኤፍ ኢ ኮንስትራክሽን Additional Administration Block ግንባታ በብር 69,258,562.56 በተገባ ውል እስከ ሚያዝያ 08/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 66% ላይ የሚገኝ ሲሆን 34% /69,258,562.56*34/100= 23,547,911.08 የቀረው በመሆኑ እና መጠናቀቅ ከነበረበት የውለታ ጊዜ ከ88 ቀን በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቱ ግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 23,547,911.08 *88*1/1000=2,072,216.17 ገቢ አለመደረጉን፣

- ፉፋ ሌጂሳ ሕ/ሥ/ተቋራጭ Dormitory G&F,Seminar Class room & Entertainment A ግንባታ በብር 140,712,398.04 በተገባ ውል እስከ ሰኔ 08/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 59% ላይ የሚገኙ ሲሆን 41% /140,712,398.04*41/100= 57,692,083.20 የቀረው በመሆኑ እና በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ22 ቀናት በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 57,692,083.20 *22*1/1000=1,269,225.83 ገቢ አለመደረጉን፣

- አበራ ማሞ ሕ/ሥ/ተቋራጭ Dormitory I ግንባታ በብር 45,531,301.54 በተገባ ውል እስከ ሰኔ 08/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 78% ላይ የሚገኝ ሲሆን 22% /45,531,301.54*22/100=10,016,886.34 የቀረው በመሆኑ እና በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ22 ቀናት በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 10,016,886.34 *22*1/1000=220,371.50 ገቢ አለመደረጉን፣

- **ደሳለኝ አያሌው ሕ/ሥ/ተቋራጭ** Seminar, Class room & Lecture Hall C ግንባታ በብር 32,655,422.60 በተገባ ውል እስከ ሰኔ 08/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 76% ላይ የሚገኙ ሲሆን 24% /32,655,422.60*24/100= 7,837,301.42 የቀረው በመሆኑ እና በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ22 ቀናት በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 7,837,301.42 *22*1/1000=172,420.63 ገቢ አለመደረጉን፣

በድምሩ ብር **10,057,217.40** የጉዳት ካሣ /Liquidation Dameg/ ገቢ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.15.2 <u>ስጋት፣</u>

- የወጣው የመንግስት የግዥ መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡
- ግንባታዎች በወቅቱ አለመጠናቀቅ በተቋሙ የመማር ማስተማር (በተማሪዎች ቅበላ፣ በተግባር ትምህርት አሠጣጥ) በሌሎችም አገልግሎቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

2.15.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በዩኒቨርሲቲው በመከናወን ላይ የሚገኙ ግንባታዎች ተጠናቀው ለተፈለጉበት ዓላማና አገልግሎት ለማዋል እንዲቻል ተቋራጮች በውል መሰረት ግንባታዎቹን አጠናቀው እንዲያስረክቡ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የጉዳት ካሳውም በውሉ መሰረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

2.15.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ለሁሉም ስራ ተቋራጮቹ አማካሪ ድርጅት ያቀረቡትን ምክንያት በማጤን የጊዜ ማራዘሚያ ተጠይቆ በማኔጅመንቱ እንዲፈቀድ ተደርጓል በመሆኑም በኦዲት ግዜ ገደብ ውስጥ ተቋራጮቹ ቅጣት ውስጥ አልገቡም የግዜ ማራዘሚያ የተሰጠበትን ማስረጃውን አያይዘናል፡፡

2.15.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በኦዲት ግዜ ገደብ ውስጥ ተቋራጮቹ ቅጣት ውስጥ አልገቡም የግዜ ማራዘሚያ የተሰጠበትን ማስረጃውን አያይዘናል ተብሎ ምላሽ ለተሰጠው የታህሳስ 2010 ዓ/ም የተደረገ የግዜ ማራዘሚያ እንጂ እስከ ሰኔ 30 2009 ዓ/ም የተደረገው የግዜ ማራዘሚያ ማስረጃ አሁን ቢሆን አልቀረበልንም፡፡ ስለሆንም በታህሳስ 2010 ዓ/ም የተደረገ የግዜ ማራዘሚያ ደግም ለ2009 ዓ/ም በጀት ዓመት መስረጃ ሊሆን ስለማይችል ተቀባይነት የለውም፡፡

3. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

3.1 ግኝት፣

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሠራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ በተጨማሪም በመመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5/መ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይሁንና የዩኒቨርሲቲው የተሰብሳቢ ሂሳብ በመመሪያው መሠረት በወቅቱ መወራረዱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰኔ 30/2009 በሪፖርቱ ከሚታየው ብር 149,265,332.23 ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 4211/የግዥ ቅድሚያ ክፍያ/ የተሰጠ ብር 2,240,568.39 ለዘጠኝ የግዥ ሰራተኞች የተሰጠ ሲሆን በደንቡ መሰረት መጀመሪያ የወሰዱትን ሳያወራርዱ በተደጋገሚ የተሰጣቸውና ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ያልተወራረደ መሆኑ፤

- በሂሳብ መደብ 4253 ለዕቃ አቅራቢዎች የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ/ Advance to supplier/ ብር 4,410,606.30 ዕቃው ገቢ ባለመደረጉ ከ6 ወር በላይ ሂሳቡ ሳይወራረድ መገኘቱን፤
- በሂሳብ መደብ 4274 / ለሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች/Other advance / የተሰጠ ብር 6,415,519.87 ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ ያልተሰበሰቡ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 13,066,694.56 በደንቡ እና በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

3.2 <u>ስጋት፣</u>

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረድ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለውን የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊያደርስ ይችላል፡፡

3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ሊወራረድ የሚችለውን እንዲወራረድ፣ ሊወራረድ የማይችለውን ደግሞ ደንቡ በሚያዘው መሠረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተቋሙ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በቅድሚያ ወጪ በሚደረጉ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- በሂሳብ መደብ 4211 የሚታየው ተማሪዎች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከገቢ ያልወጡ በመሆኑ ለስኳር፤ ለዘይትና ለተለያዩ የምግብ አቅርቦት በግዥ ሰራተኞች ስም የነበረ ሲሆን እስከ ነሀሴ 30/2009 እንዲወራረድ ተደርጓል፡፡
- በሂሳብ መደብ 4274 ያለው የእያንዳንዱ ሰራተኛ ከማን ምን እንደሚፈለግ በግልጽ የሚታወቅ በመሆኑ ተሰብሳቢውን የማጥራት እና የሚሰበሰበው ተለይቶ በሰነድ እና በጥሬ ገንዘብ የሚከፈለውን በመለየት የማወራረድ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

- በሂሳብ መደብ 4253 እቃው በውሉ ጊዜው ገቢ ቢደረግም በተለያዩ ቴክኒክ ኮሚቴዎች ጥራታቸው ተረጋግጦ ክፍያ መፈጸም ባለመቻሉ ሲሆን በወቅቱም የባንክ ዋስትናው ጊዜ ገደቡ እንዳያልፍ ክትትል ተደርጓል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ተወራርዷል፡፡

4. የተከፋይ ሂሳብ፣

4.1 ግኝት፣

የተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ የተከፈሉ ወይም የተወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሂሳብ መደብ በ5028 በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች /Other payables within government /በሰኔ 30/2009 በሪፖርት የሚታየው ብር 515,142.50 በተከፋይ የተያዘ እና ለtufts universeity መከፈል የሚገባው ለባለመብቱ ሳይከፈል ከአንድ ዓመት በላይ መቆየቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

4.2 ስጋት፣

የተከፋይ ሂሳብ ለባለመብቱ ድርጅት፣ መ/ቤት ወይም ግለሰብ በወቅቱ አለመተላለፉ ገንዘቡ ለታቀደለት ዓላማ እንዳይውልና በበጀት አጠቃቀም ላይም ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ለወደፊቱም የተከፋይ ሂሳብ ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የtufts universeity አደራ ሂሳብ ሲሆን ሙሉ መረጃውን በማጠናቀር ሰነዱን ለተቋሙ እንዲላክ ይደረጋል ተመራማሪዎቹ በተለያየ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ በመሆኑ ነው ዋናው ተመራማሪ የዩኒቨርሲቲው መምህር ስለሆነ ግዜ ገደብ ተሰጥቶት እንዲያቀርብ እናደርጋለን፡፡

5. በጀት፣

5.1 ግኝት፣

የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሦስት ተራ ቁጥር 02(1) ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንደሚገባው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተመደበው የወጪ በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር በየፕሮግራሞቹ ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 1,577,288.80 ያልተሰራበት በጀት መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፣

የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት እስከ ሰኔ 30/2009		ሥራ ላይ የዋለ በጀት እስከ ሰኔ 30/2009		ያልተሰራበት በጀት እስከ ሰኔ 30/2009		ያልተሰራ በት በጀት በመቶኛ (%)
6113	386,000	00	-		386,000	00	100
6133	50,160	00	28,471	44	21,681	56	43.22
6223	5,403,038	00	4,233,430	76	1,169,607	24	21.65
ድምር	**5,839,198**	**00**	**4,261,909**	**20**	**1,577,288**	**80**	

5.2 ስጋት፣

ዩኒቨርሲቲው የበጀት አጠቀቀምና አያያዝ ስርዓቱ በአግባቡ ካልተጠቀመ ዓመታዊ ዕቅዱን ሊያዛባ ከመቻሉም በላይ በሌሎች መ/ቤት /ተቋማት/ ሊሰራበት የሚችለውን በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ይሆናል።

5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በየወሩ በሥራ ክፍሉ በሚቀርበው የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት መሠረት ተራፊውን በጀት በመ/ቤቱ ስም ተይዞ እንዳይቆይ በሌሎች መ/ቤቶች እንዲሰራበት ሪፖርት

እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተቋሙ የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስና በጀት አዋጅ መሠረት መጠቀም ይኖርበታል፡፡

5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ዩኒቨርሲቲው ካሉት አራት ፕሮግራሞች በተለይም በ6113 የኮንትራት ሰራተኛ ፍቃድ ባለመኖሩ በ6114 ሲከፈል የነበረ ነው፡፡ በ6133 ለዚሁ መደብ ለሚቀጠሩ ሰራተኞች የጡረታ መዋጮ ነው፡፡ ሌላው በ6223 ያለው የምርምር በጀት ተመራማሪዎች በወቅቱ ስራቸውን ስለማይጨርሱ በ4274 ከሚገኘው ተሰብሳቢ የአንበሳውን ድርሻ ከመውሰዱም አንዱ ሲሆን በወቅቱ ባለመወራረዱ በበጀት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ አስደርጓል፡፡ በቀጣዩ አጠናክረን ለመስራት ከወዲሁ ዘርፉ በፕሬዝዳንት የተዋቀረ ስለሆነ በትኩረት እንዲሰራበት ይደረጋል፡፡

6. ንብረት፣

6.1.1 ግኝት፣

በፌዴራል መንግስት አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ ፤የመጠቀም ፤የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንደሚገባ በአዋጁና በመመሪያው ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ አወጁንና መመሪያውን መሰረት በማድረግ የንብረት አመዘጋገብ ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡

- **የአላቂ እቃዎች ግምጃ ቤትን በተመለከት**

  በግምጃ ቤቱ ውስጥ ቢን ካርድም ሆነ ስቶክ ካርድ ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆኑ እንዲሁም የንብረት ቁጥጥርና ምዝገባ ባለሙያ የሌለ በመሆኑ የአላቂ እቃዎችን የማመዛዘን ስራ እየተሰራ አለመሆኑ፡፡ በተጨማሪም አገልግሎት መስጠት የሚችሉ እቃዎችና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ እቃዎች በአንድ ላይ ለብልሽት በሚዳርግ አቀማመጥ ተደበላልቀው የተቀመጡ መሆኑ፡፡ እንዲሁም ተመሰሳይ የሆኑ እቃዎች በተለያየ ቦታ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡

በ2006 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ከ2000 በላይ ዊንዶ ክሊነሮች የአገልግሎት ጊዜያቸው እኤአ ጥር 2017 ዓ.ም የሚያበቃ እያሉ እና እነሱን ጥቅም ላይ አውሎ ሲያልቁ ሌላ ተጨማሪ መግዛት ሲገባ በ2009 ዓ.ም እና በ2010 ዓ.ም እጅግ በርካታ ዊንዶ ክሊነሮች እንዲገዙ በመደረጉ ቀደመው የተገዙት ከ2000 በላይ ጥቅም ላይ ሳይውሉ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መኖራቸው፡፡ እንዲሁም ግዥው እንዲገዛላቸው ለጠየቁት የስራ ክፍሎች በማሳወቅ ወጪ እንዲሆን ማደረግ ሲገባ ባለመደረጉ በተጨማሪ የተገዙትም ቢሆን ወጪ እየተደረጉ አለመሆኑ ለተጨማሪ ብልሽት የሚዳርግ አሰራር እየተሰራ መሆኑ፡፡

በ2006 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ 3450 የወረቀት መብሻ ሪንጎች ግዥው እንዲገዛላቸው ለጠየቁት የስራ ክፍሎች ወጪ ተደርገው ጥቅም ላይ ሳይውሉ በ2010 ዓ.ም ሌላ ተገዝቶ ወደ ግምጃ ቤቱ ገቢ የተደረገ መኖሩ፣ በ2006 ዓ.ም ለደንብ ልብስ ተብለው ተገዝተው ገቢ የተደረጉ 300 የሴቶች ሸሚዞች ፣ 32 ጥንድ የሴቶች ጫማዎች ፣ 375 ሜትር ጣቃ ጨርቅ ፣ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በግምጃ ቤቱ ውስጥ መገኘታቸው ፣

በ2008 ዓ.ም ተገዝቶ ገቢ የተደረገ 12384 ዳና የገላ ሳሙና እያለ ለሰራተኛው ሌላ ሳሙና ተገዝቶ በመሰጠቱ ያለመፍትሄ በግምጃ ቤቱ ውስጥ የተቀመጠ መሆኑ፣ በ2009 ዓ.ም ተገዝቶ ገቢ የተደረገ 166600 ክላሰር ግዥው እንዲገዛለት ለጠየቀው የስራ ክፍል ወጪ እየተደረገ ባለመሰጠጡ በክምችት ላይ የሚገኝ መሆኑ ፣ በ2008 ዓ.ም ተገዝቶ ገቢ የተደረገ ከ300 በላይ የብረት ባልዲ ለውሃ መቅጃ አገልግሎት የሚውል እያለ በ2010 ዓ.ም እጅግ በርካታ የብረት ባልዲዎች ተገዝተው ገቢ የተደረጉ መሆኑ እና ቀድሞ የተገዙት ባለዲዎችም ጥቅም ላይ እየዋሉ አለመሆናቸው፡፡

በ2006 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ከ6310 በላይ አግራፎች ወጪ ተደርገው ጥቅም ላይ ሳይውሉ መገኘታቸው ፣ በ2007 ዓ.ም ተገዝቶ ገቢ የተደረገ ከ600 በላይ ጥቅል የእቃ ማጠቢያ ሽቦ ጥቅም ላይ ውሎ ሳያልቅ በ2010 ዓ.ም ሌላ የተገዛ መኖሩ፣

በ2009 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ከ300 በላይ የሚሆኑ ለስራ ክፍሎች አገልግሎት የሚውሉ የበር ምንጣፎች (ዌል ካም ምንጣፎች) አገልግሎት ላይ ሳይውሉ በ2010 ዓ.ም እጅግ በርካታ ምንጣፎች የተገዙ መሆኑ፡፡

በ2008 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ሜሪት ዲክሽነሪ ባለ 44000 ቃላት ብዛት 48 እና ኢሊሴ ዲክሽነሪ ባለ 93000 ቃላት ብዛት 48 ፣ በ2009 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ 14 የሽንት ቤት ሳህኖች ፣ በ2008 ዓ.ም ተገዝቶ ገቢ የተደረጉ 24 ከበርሜል የተሰሩ የልብስ ማጠቢያዎች ግዥው ለጠየቀው ክፍል ወጪ ተደርገው አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መገኘታቸው፡፡

በ2008 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ብራዘር የፕሪንተር ቀለሞች ሞዴል Hl 5440 ብዛት 80፣ የሻይ ማፍሊያ ማንቆርቆሪያ ትንሿ ብዛት 504 ግዥው እንዲገዛላቸው ለጠየቁት የስራ ክፍሎ ወጪ ተደርጎ አገልግሎት ላይ ያልዋለ መሆኑ፡፡

በ2009 ዓ.ም ወጪ የተደረገ ችፑድ ብዛት 120 ፣ በ2008 ዓ.ም ወጪ የተደረገ ቆርቆሮ ብዛት 40 ወጪ ያደረገው አካል ጥቅም ላይ ሳያውለው በእቃ ግምጃ ቤቱ ውስጥ ያለ መሆኑ፡፡

ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበት (የተበላሸ) 12 ከረጢት ሲሚንቶ ፣ለናሙና የመጡ የተለያዩ ፍራሾች ብዛት ከ20 በላይ ያለመፍትሄ ከ2 ዓመት በላይ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡

በ2008 ዓ.ም ለናሙና የመጡ እጅግ ብዛት ያላቸው የተለያዩ እቃዎች ያለመፍትሄ ተከማችተው በእቃ ግምጃ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፡፡

በ2010 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ የአገልግሎት ጊዜያቸው እኤአ ሰኔ 2018 የሚያበቃ ማላታይን ፀረነፍሳት ኬሚካል ብዛት 300፣ ሶዲየም ፕሮሰስ ኬሚካል ባለ 50 ኪሎ ግራም ብዛት 2 ግዥው እንዲገዛለት ለጠየቀው የስራ ክፍል ወጪ ተደርገው አገልግሎት ላይ ሳይውሉ በአላቂ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ከሌሎች እቃዎች ጋር ተቀላቅሎ የተቀመጠ መሆኑ፡፡ ይህም በአላቂ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የእሳት አደጋ ሊያስነሳ በሚችል አቀማመጥ የተቀመጠ በመሆኑ

መንግስት በብዙ ሚሊየኖች ለገዛቸው እቃዎችና ለገነባው ግምጃ ቤት መውደም ምክንያት በሚሆን አቀማመጥ የተቀመጠ መሆኑ፡፡

- **የቋሚ እቃዎች ግምጃ ቤትን በተመለከት**

ለዩኒቨርሲቲው ለቋሚ ዕቃ ንብረት በከፊል መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑን በግምጃ ቤቱ ውስጥ ቢን ካርድም ሆነ ስቶክ ካርድ ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆኑ እንዲሁም የንብረት ቁጥጥርና ምዝገባ ባለሙያ የሌለ በመሆኑ የቋሚ እቃዎችን የማመዛዘን ስራ እየተሰራ አለመሆኑ ፡፡

በ2009 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ቴብል ቴነስ ቦርድ ብዛት 5 ፣ ዲጂታል ፖዲየም የአይሲቲ እቃዎች በትላልቅ 4 የእንጨት ሳጥኖች ውስጥ ታሽገው የተቀመጡ ፣ ብዛት ያላቸው የካፍቴሪያ ቴብሎች (ኮፊ ቴብሎች) ፣ ፍሪጆች ብዛት 8 ግዥው እንዲገዛላቸው ለጠየቁ የስራ ክፍሎች ወጪ ተደርጎ መሰጠት ሲገባ አገልግሎት ላይ ሳይውሉ በግምጃ ቤቱ ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡

በቀን 1/09/09 ተገዝተው ገቢ የሆኑ 28 የግድግዳ ሰዓቶች ፣ በቀን 23/05/09 ተገዝተው ገቢ የተደረጉ 85 ፕሮጀክተሮች ፣ በቀን 7/03/09 ተገዝተው ገቢ የተደረጉ 7 ፋክስ ማሽኖች ፣ በቀን 21/5/09 ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ብዛት ያላቸው ዲሲ ፓወር ሰፕላየሮች ሞዴል1621A ግዥው እንዲገዛላቸው ለጠየቁ የስራ ክፍሎች ወጪ ተደርገው ጥቅም ላይ ሳይውሉ በግምጃ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፡፡

አገልግሎት የማይሰጡ (የተሰባበሩ) ብዛት ያላቸው የቢሮ ጠረጴዛዎች ያለመፍትሄ ከአዲስ ቋሚ እቃዎች ጋር በግምጃ ቤቱ ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡ እንዲሁም የሴሌዳ ቁጥር የሌላቸው 2 ቲቪኤስ ሞተር ሳይክሎች አገልግሎት ላይ መዋል ሲገባቸው ያለአገልግሎት በእቃ ግምጃ ቤቱ ውስጥ ያሉ መሆኑ፡፡

- **የጥገና እና እድሳት ግምጃ ቤትን በተመለከተ**

ቢን ካርድና እስቶክ ካርድ የማይጠቀሙ መሆኑ ፡፡ የንብረት ቁጥጥርና ምዝገባ ባለሙያ የሌለ በመሆኑ ስቶክ የማመዛዘን ስራ ያልተሰራ መሆኑ፡፡

የግምጃ ቤት ጥበት በመኖሩ የኤሌክተርክ ፣ የቧንቧ እና ሌሎች የጥገና እና እድሳት መለዋወጫ እቃዎች ለብልሽት በሚዳርግ አቀማመጥ ተደበላልቀው የተቀመጡ መሆኑ፡

- **የመኪና መለዋዎጫ እቃዎች ግምጃ ቤትን በተመለከተ**

  ቢን ካርድና እስቶክ ካርድ የማይጠቀሙ መሆኑ ፡፡ የንብረት ቁጥጥርና ምዝገባ ባለሙያ የሌለ በመሆኑ ስቶክ የማመዛዘን ስራ ያልተሰራ መሆኑ፡፡

  በ2007 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ከ60 በላይ አዳዲስ ጎማዎች የጥራት ችግር አለባቸው በሚል አገልግሎት ላይ ሳይውሉ በግምጃ ቤቱ እያሉ ሌላ ጎማ እየተገዛ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑ፡፡ እንዲሁም በሌላ ጠባብ የሽንት ቤት ክፍል ውስጥ ብዛት ያላቸው የመኪና መለዋወጫ እቃዎች ለብልሽት በሚዳርግ አቀማመጥ ተደበላልቀው የተቀመጡ መሆኑ፡፡

- **ተመላሽ እቃ ግምጃ ቤትን በተመለከተ**

  ዩኒቨርስቲው ከተቋቋመ ጀምሮ ተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት አይሰጡም ተብሎ የተመለሱ በርካታ ንብረቶች ተከማችተው የሚገኙና ያልተወገዱ መሆኑ፣ የመኪና ጎማ ብዛት ከ400 በላይ እጅግ በርካታ የመኪና መለዋወጫዎች ፣ 3 ዲሾች ፣ ከ300 በላይ ወንበሮች ፣ ብዛት ያላቸው የአይሲቲ እቃዎች ፍላት ኤል ጂ ቴሌቪዥን ብዛት 1 ፣ላፕቶፕ ኮምፒተሮች ብዛት 35 ፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን ብዛት 2 ፣ ብዛት ያላቸው ተመላሽ የመኪና ባትሪዎች እንዲሁም ሌሎች በርካታ ልዩ ልዩ የቢሮ ዕቃዎች በጠባብ ክፍሎች ውስጥ ለመለየት በሚያስቸግር አቀማመጥ ተደራርበውና ተደበላልቀው የተቀመጡ መሆኑ፡፡

- **ሌሎች**

  በቋሚ እና አላቂ ግምጃ ቤቶች አካባቢ ትምህትር ሚኒስቴር ዩኒቨርስቲው ሲቋቋም ለግንባታ ያመጣቸው በጣም በርካታ ፌሮዎችና ትልልቅ ጥቅል ሽቦዎች አገልግሎት ላይ ሳይውሉ ወይንም መፍትሄ ሳይሰጣቸው ሜዳ ላይ በየቦታው ያሉ መሆኑ፡፡ እንዲሁም በዩኒቨርስቲው ግቢ መግቢያ ባለ በጤፍ ግምጃ ቤት

በር ፊት ለፊት በርካታ አሮጌ የእንጀራ መጋገሪያ ምድጃዎች ሳይወገዱ ያሉ መሆኑ::

- **<u>የተማሪዎች የምግብ ጥሬቃዎች ፣ የማብሰያ እቃዎች እና የመመገቢያ እቃዎች አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከት</u>**

  - የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ለተግባር ትምህርት መስክ በሚሄዱበት ጊዜ አካዳሚክ ትምህርት ክፍሉ ለመስክ የሚሄዱ ተማሪዎችን ቁጥር ፣ ከመቼ ጀምሮ እንደሚሄዱ እና የመስክ የቆይታ ጊዜያቸውን እና የመመለሻ ጊዜያቸውን ጭምር በወቅቱ ለተማሪዎች ምግብ ቤት ስለማያሳውቅ ምግብ ከተሰራ በኋላ በመትረፍ እየተበላሸ መሆኑ እና ተማሪዎች መስክ ወጥተው ይቆያሉ ከተባለው ጊዜ ቀድመው ሲመለሱም ካፌ የሚጠቀሙ በመሆኑ ይህም ዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ መስክ ሲወጡ በቀን ከሚከፍላቸው የምግብ ወጪ በተጨማሪ ያላግባብ ምግብ እየተሰራ በመሆኑ ዩኒቨርስቲውን ለተጨማሪ ወጪ እየዳረገው መሆኑ፡፡
  - ሁሉም የተማሪዎች ምግብ ቤት የጥሬ እቃ ግምጃ ቤቶች ቢንካርድና ስቶክ ካርድ የሌላቸው መሆኑ ባለሙያዎቹም የቢን ካርድና የስቶክ ካርድ እውቀት የሌላቸው መሆኑ እንዲሁም የምግብ ጥሬ እቃዎችን ስቶክ የሚቆጣጠር የቁጥጥርና ምዝገባ ባለሙያም ባለመኖሩ የቁጥጥር ስራ እየተሰራ ስላልሆነ የኒቨርስቲውን ለተጨማሪ ወጪ እየዳረገው መሆኑ፡፡
  - የተማሪዎች የምግብ ጥሬ እቃዎች ወጪ ተደርገው ምግብ ለሚያበስሉ የስራ ክፍሎች መሰጠት ያለባቸው ከተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር እና ከተማሪዎች ምግብ ቤት ኃላፊ በተማሪዎች ቁጥር ልክ የቀን የምግብ ፈጆታቸውን መሰረት ያደረገ ደብዳቤ እና ሞዴል 20 ተፈርሞበት ለሚመለከታቸው የምግብ ጥሬ እቃዎች ግምጃ ቤቶች ባለሙያዎች በማሳወቅ መሆን ሲገባ ምግብ የሚያበስሉ ክፍሎችን

የሚያስተባብሩ የሽፍት ኃላፊዎች በቃል በሚጠይቁት ጥያቄ ብቻ የተማሪዎችን ቁጥር መሰረት ያላደረገ የምግብ ጥሬ እቃ ወጪ እየተደረገ በመሆኑ ዩኒቨርስቲውን ለምግብ ብክነትና ለተጨማሪ ወጪ እየዳረገው ያለ አሰራር እየተሰራ መሆኑ፡፡

- ዩኒቨርስቲው የተማሪዎችን የምግብ ጤፍ አስፈጭቶ የሚያቀርብ አካል በጨረታ አወዳድሮ አሸናፊውን በመለየት ከአንድ ኩንታል ጤፍ ላይ በአማካኝ ንፋሽና ብጣሪ ወጥቶለት ቀሪውን በማስፈጨት ለዩንቨርስቲው ተማሪዎች ምግብ ቤት ዱቄት ክፍል እየተመዘነ የተማሪዎች ተወካዮች በተገኙበት በርክክብ ለመቀበል ውል የተዋዋለ ሲሆን ፣ ነገር ግን እየተሰራ ያለው ዱቄት ተፈጭቶ ሲመጣ በውሉ መሰረት በትክክል መዝኖ (ኪሎግራሙን አረጋግጦ) መረከብ ሲገባ አቅራቢው ጤፍ ለማስፈጨት የወሰደውን ኩንታል ቁጥር መሰረት በማድረግ ብቻ እርክክብ የሚፈፀም መሆኑ፡፡
- በጤፍ ግምጃ ቤት ውስጥ በጥራት ጉድለት ምክንያት በሚል መፍትሄ ያልተሰጠው የተበላሸ 34 ኩንታል ጤፍ ካልተበላሸ ጤፍ ጋር ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፡፡
- ዩኒቨርስቲው ሲቋቋም ለተማሪዎች የምግብ ማብሰያ የሚሆኑ በትምህርት ሚኒስቴር ተገዝተው የተሰጡ የሻይ ማፍሊያ ቦይለሮች ብዛት 8 ፣ፍሪጆች ብዛት 9 ፣ የምግብ ማብሰያ እስቶቦች ባለ አራት ምድጃ ብዛት 6 ፣ ባለ ሁለት ምድጃ ብዛት 2 ፣ የጋዝ ሲሊንደሮች ብዛት 4 ፣ የስጋ መፍጫ ብዛት 2 እና ሌሎችም በብልሽት ምክንያት ተጠግነው አገልግሎት ላይ ሳይውሉ ወይንም ሳይወገዱ ከ3 ዓመት በላይ ያለመፍትሄ በተማሪዎች ምግብ ማብሰያ ክፍል ውስጥ ያሉ መሆኑ፡፡
- በዘይት ግምጃ ቤት ውስጥ እጅግ በርካታ አዳዲስ የመመገቢያ ሹካዎች፣ የመመገቢያ ሳህኖች፣ የሻይ ማንቆርቆሪያዎች እና ጭልፋዎች አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ መሆኑ፡፡

- በተማሪዎች የምግብ ማብሰያ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ አገልግሎት የሰጡ የፕላስቲክ በርሜሎች ብዛት 54 ፣ እጅግ በጣም ብዛት ያላቸው የመመገቢያ ሳህኖች ፣ የፕላስቲክ የሻይ ኩባያዎች ፣ ትንንሽ የምግብ ማብሰያዎች ፣ የመመገቢያ ሳህኖች እና ሌሎችም በርካታ እቃዎች አገልግሎት ከሚሰጡ ከሌሎች እቃዎች ጋር ለበለጠ ብልሽት በሚዳርግ አቀማመጥ ተደበላልቀው ከ2 ዓመት በላይ ያለመፍትሄ የተቀመጡ መሆኑ ፡፡

- **<u>የተማሪዎች ክሊኒክን በተመለከተ</u>**

  - በክሊኒኩ ዋና ግምጃ ቤት ውስጥ ቢን ካርድ ያለ ቢሆንም መድሀኒቶቹ በተቀመጡበት ስፍራ ያልተቀመጠና መድሀኒቶች ገቢና ወጪ በሚሆኑበት ጊዜ ቢንካርድ ወቅቱን ጠብቆ ያልተመዛዘነ /አብዴት/ ያልተደረገ መሆኑ፡፡ የመድሀኒት ቁጥጥርና ምዝገባ ባለሙያ የሌለ በመሆኑ ስቶክ የማመዛዘን ስራ ያልተሰራ መሆኑ፡፡ እንዲሁም መድሀኒቶች የሚቀመጡበት የቦታ (የግምጃ ቤት) ጥበት በመኖሩ መድሀኒቶችን ለብልሽት ሊዳርግ በሚችል አቀማመጥ በአቧራማ ጠባብ ክፍል ውስጥ ተደራርበውና ተደበላልቀው መሬት ላይ ጭምር የተቀመጡ መሆኑ፡፡
  - በመድሃኒት ማሰራጫ /በዲስፔንሰሪ / ክፍል ውስጥ ቢንካርድ የሚጠቀሙ ሲሆን ነገር ግን መድሀኒቶች ገቢና ወጪ በሚሆኑበት ጊዜ ቢንካርድ ወቅቱን ጠብቆ ያልተመዛዘነ /አብዴት/ ያልተደረገ መሆኑ፡፡ በተጨማሪም የክፍሉ ጠባብ መሆን መድሀኒቶችን ለብልሽት በሚዳርግ አቀማመጥ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡
  - በክሊኩ አካባቢ ያሉ ክፍሎች ለገቢ ማመንጫ በሚል ለተለያዩ ማህበራት ለሱፐር ማርኬት ፣ ለስቴሽነሪ እቃዎች ፣ ለወንዶችና ለሴቶች የውበት ሳሎኖች እና ለሸቀጣሸቀጥ መሸጫ ሱቅ በመከራየታቸው ክሊኒኩ በስራ ክፍሎች ጥበት ምክንያት በአግባቡ ስራዎችን እየሰራ አለመሆኑ ፡፡ እንዲሁም በጤና ህጉ መሰረት ተለያይተው መሰራት ያለባቸውን ስራዎች

በአንድ ክፍል ውስጥ ተጨናንቀው ለመስራት ያስገደዳቸው መሆኑ፡፡ በተጨማሪም በነዚሁ ለገቢ ማመንጫ ተብለው ከተከራዩ ክፍሎች አገልግሎት ለማግኘት ከሚመጡ ተማሪዎች የሚወጡ ከፍተኛ ድምፆች እና ከተከራዮቹ ከሚወጡ ቆሻሻዎች ታካሚ ተማሪዎችን እና የክሊኒኩን ሰራተኞችን የሚረብሹና ለጉዳት እየዳረጓቸው መሆኑ፡፡ ይህንኑ በማስመልከት በ2008 ዓ.ም በዋና ኦዲተር መ/ቤት በኦዲት ግኝት ወጥቶ አሰራሩ እንዲስተካከል የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት እና ክሊኒኩ ችግሩ እንዲፈታለት ለአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዝዳንት በደብዳቤ ቢያሳውቅም እስከአሁን ምንም አይነት መፍትሄ ያልተሰጠው መሆኑ፡፡

- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ እጅግ በርካታ መድሀኒቶች በዋናው የመድሀኒት ክፍል ውስጥ ሳይወገዱ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ሌሎች መድሀኒቶችን ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ አገልግሎት ከሚሰጡ መድሀኒቶች ጋር ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑ፡፡
- የህክምና መሳሪያዎች የሚፀዱበት (የሚቀቀሉበት) አውቶ ክሌፍ መሳሪያ ብዛት 2 በብልሽት ምክንያት ከ2 ዓመት በላይ ተጠግነው አገልግሎት ላይ ሳይውሉ ወይንም ሳይወገዱ በዋናው የመድሀኒት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

6.1.2 ስጋት፣

ዩኒቨርሲቲዉ በንብረት አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተገለፁት ሁኔታዎች እና ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የማያደርግ ከሆነ የዩኒቨርሲቲዉ ንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅና አመዘጋገብ ለበለጠ ጥፋት ሊጋለጥ ይችላል፡፡ መንግስትንም ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

6.1.3 ማሻሻያ ሀሳብ፣

ከላይ በዝርዝር በተገለፁት የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅ በኩል በታዩት ድክመቶች ላይ የሥራ አመራሩ ተገቢውን ክትትል በማድረግ በአግባቡ ባለመቀመጣቸው ለብልሽት በመዳረግ ላይ የሚገኙት ንብረቶች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ እና ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶች ላይም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- **አላቂ እቃዎችን በተመለከተ**

አላቂ ስቶርን በተመለከተ ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ በርክክብ ወቅት በተፈጸመ መዘናጋት የተወሰነ ውስንንት ቢኖረውም ካርዶቹ በስራ ላይ ያሉ መሆናቸው፡፡ የንብረት ቁጥጥርና ምዝገባ ባለሙያ በአዲሱም ሆን በበፊቱ መዋቅርም ያለ ቢሆንም የማመዛዘን ስራውን እንዲሰሩ ክትትል እናደርጋለን፤የአገልግሎት ግዜ ያለፈባቸውን እቃዎች ኮሚቴ በማቋቋም በደንቡ መሰረት እንዲወገዱ እናደርጋለን፡፡

- **ቋሚ እቃዎችን በሚመለከት**

ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ በስርአቱ እንዲተገበር እናደርጋለን በአሁኑ ሰአትም ስራው ተጀምሯል፤በንብረት ክፍል የሚገኙትን ቋሚ እቃዎች ለስራ ክፍሎች እንዲደርሱ እናደርጋለን፤አገልግሎት የማይሰጡ እቃዎችን ወደ አሮጌ ንብረት ክፍል እናስገባለን፤ሞተር ሳይክሎችን በተመለከተ ታርጋ ወጥቶላቸው ወደ ስራ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

- **የጥገና እና እድሳት ግምጃ ቤት በተመለከተ**

የንብረት ቁጥጥር ሰራተኛ እጥረት ስለ አለ እና ስራውን የሚያሰራው ክፍል የፋሲሊቲ አስተዳደር በመሆኑ በክፍሉ በኩል ቁጥጥር እንዲደረግ እና ጥያቄም ሲቀርብ የአጠቃቀም ሪፖርት እንዲቀርብ እናደርጋለን፡፡

- **የመኪና መለዋወጫ እቃዎች ግምጃ ቤትን በተመለከተ**

የንብረት ቁጥጥር ሰራተኛ እንዲመደብ እና ወደ ስራ እንዲገባ እናደርጋለን ለዚህም የቅጥር ማስታወቂያ አውጥተናል በቅርቡ ሰው ቀጥረን ቁጥጥሩን እናጠናክራለን፡፡

- **ተመላሽ እቃ ግምጃ ቤትን በተመለከተ**

የሚወገዱ ማቴሪያሎችን በተመለከተ በተለይ ቁርጥራጭ ብረታብረቶች፤ እንዳናስወግድ መመሪያ ስለሚያግደን ነው የመኪና ጎማዎች፤ ባትሪዎች፤ የፎቶ ኮፒና የፕሪንተር ቀለሞች፤ ኬሚካሎችና ሌሎችም በደንቡ መሰረት እናስወግዳለን፡፡

ፊሮዎች እና ብረታ ብረቶች ለአገልግሎት በሚፈለጉበት ወቅት ለአገልግሎት እንዲውሉ በአግባቡ እንዲሰበሰቡ እና እንዲቀመጡ እናደርጋለን፡፡

- **የክሊኒክ በተመለከተ**

ክልኒክን በተመለከተ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ በወቅቱ እንዲመዘገብ እና ክትትል ይደረጋል፤የመጠቀሚያ ግዚአቸው ያለፈ መድሃኒትን በተመለከተ በደንቡ መሰረት እንዲወገድ መረጃውን አተናቅረን እናስወግዳለን፡፡ እንዲሁም በቀጣይ የእራሱ ህንጻ እንዲኖረው ይደረጋል፤አውቶክሌቭን በተመለከተ ተደጋጋሚ ጥገና ተደርጎለት ለአገልግሎት አስቸጋሪ ስለሆነ በደንቡ መሰረት እንዲወገድ እናደርጋለን፤የመድሃኒት ክፍል ጥበትን በተመለከተ ከሚመለከተው ስራ ክፍል ጋር በመሆን መፍትሄ እንዲፈለግ ይደረጋል፡፡

- **የተማሪዎች ምግብ ቤት ጥሬ እቃዎች አያያዝ እና አጠቃቀም፡፡**

የተማሪዎች የመስክ ቆይታ ግዜን ኮሌጆች ለተማሪዎች አገልግሎት እንዲያሳውቁ የደረጋል ለጉዳየም ትኩረት ተሰጥቶት ክትትል እናደርጋለን፤የጤፍ ዱቄት ርክክብን በተመለከተ ማስተካከያዎች እናደርጋለን መወገድ የሚገባቸውን እናስወግዳለን፤ የሻይ ማፊያ ማሽኖች አብዛኞቹ በሲሊነደር የሚሰሩ በመሆኑ ለአጠቃቀም አስቸጋሪ በመሆናቸው አገልግሎት ላይ ለማዋል ተቸግረናል፡፡ ክልኒክን በተመለከተ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ በወቅቱ እንዲመዘገብ እና ክትትል ይደረጋል፤ክሊኒኩ በቀጣይ የእራሱ ህንጻ እንዲኖረው ይደረጋል

- ሌሎችን የማሻሻያ ሃሳቦች ተቀብለናል በቀጣይም ስራ ላይ እናውላለን፡፡

6.2.1 ግኝት፣ ተሸከርካሪን በተመለከተ

የፌደራል መንግስት የተሸከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ፣ ዘይት እና ቅባት ፍጆታ መጠን፣ የጥገና ወጪ፣ የተጓዘው ኪ/ሜ መጠን በእነማን ስር እንደነበር ….ወዘተ እና ሌሎችም አካቶ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪ መኪናዎች አስተዳደር ኦዲት ሲደረግ፡-

- ዩኒቨርሲቲው ካሉት 36 ተሽከርካሪ መኪናዎች እና 11 ሞተር ሳይክሎች ውስጥ በኪ/ሜትር የሚጠቀሙት ነዳጅ ከልኬቱ ጋር ሲመዛዘን 15 ተሽከርካሪ በመብለጥ እና 14 ተሽከርካሪ በማነስ የሚያሳይ በመሆኑ ልኬቱን በትክክል እንደማይሰራ የተገኘ መሆኑን፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-17353 ታታ አውቶቡስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-16646 ሳን ሎንግ አውቶቡስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-21246 ሳን ሎንግ አውቶቡስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-17625 ሚኒ ባስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-17393 ሚኒ ባስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-16653 ቶዮታ ላንድ ክሩዘር፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-16692 ፒክ አፕ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-16693 ፒክ አፕ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-16687 ፓጃሮ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-2100, 2101እና 2102 ሞተር ሳይክሎች ብዛት 12 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌላቸው መሆኑን፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-16021 ዳዎ አውቶቡስ የሰሌዳ ቁጥር 4-1221 ሞተር ሳይክል የሰሌዳ ቁጥር 4-2102 ሞተር ሳይክል የነዳጅ መቁጠሪያ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ ታውቋል::

6.2.2 <u>ስጋት፣</u>

የተሽከርካሪ መረጃ አያያዝ ማለትም የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች በኪ/ሜትር የሚጠቀሙት ነዳጅ በአግባቡ እየተመዘገበ፤ ሂሳቡ እየተሰላ እና እየተቀናነሰ የሚረጋገጥበት አሰራር በተገቢው መልኩ ታሳቢ ካልተደረገ መንግስት ለነዳጅ የሚያወጣው ወጪ ለብክነት ሊዳረግ የሚችል እና ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጥ ሊያደርግ ይችላል በተጨማሪም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር አለመኖር ንብረቱ የተቋሙ ላይሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ከመቻሉም በላይ የነዳጅ ጌጅ ሳይሰራ ተሽከርካሪን አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ የነዳጅ ብክነት ሊከሰት ይችላል።

6.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የተሽከርካሪ የነዳጅ ልኬት ከሚመለከተው መ/ቤት ጋር በመመካከር በባለሙያ የተደገፈ ትክክለኛ አንድ መኪና በአንድ በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚሄድ ታውቆ በሱ መሰረት ስሌቱ መሰራት ይኖርበታል:: የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ የሌላቸውም

እንዲወጣላቸው በተጨማሪም የነዳጅ ጌጃቸው የማይሰሩ ተሽከርካሪ መኪናዎች የሚስተካከልበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል።

6.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ከኪሎ ሜትር ጋር ተያይዞ የመጨመርና የማነስ ምክንያት የሚያሳዩት የሚጨምሩት አንዳንድ የተሽከርካሪ አይነቶች ለተለያዩ ጉዳዮች ለመንግስት ስራ እንዲሁም ለደህንነት ስራዎችና በተለያዩ ጊዜ በውሰት ሲጠቀሙ የተዋሱት አካላት በራሳቸው ነዳጅ ወጪ ስለሚጠቀሙ ኪሎ ሜትሩ የመውጣትና የመውረድ ሁኔታ ያሳያል። በማነስ የሚያሳየው የኖርማላይዜሽን /የልኬት/ አጠቃቀም ላይ ተያይዞ የበፊት ልኬት አጠቃቀም ላይ የነበረው ክፍተት ተጽዕኖ ምክንያት ሊያንስ ችሏል በቀታይ እናስተካክላለን።

የባለቤትነት መታወቂያ /ሊብሬ የሌላቸውን በተመለከተ ሶስቱ ሞተር ሳይክሎች አዲስ እንደመሆናቸውና የሰሌዳ ቁጥሩም ቡሌ ሆራ ማውጣት ስለማይቻል ከሃዋሳ እንዲወጣ ፕሮሰስ ተደርጎ ስላለቀ ማቅረብ ይቻላል። የተቀሩት ተሽከርካሪዎች ግን ለሚመለከተው አካል እንዲሰጠን በቀን 15/07/09 ለመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ አዲስ አበባ እና ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አገልግሎት አዲስ አበባ ፕሮሰስ ተጀምሮ በቀጠሮ ላይ ነው ክትትል አድርገን እንጨርሳለን።

ሁለት ሞተር ሳይክሎች በብልሽት እና በአደጋ ምክንያት የተወገዱ ስለሆኑ ነው ጌጃቸው የማይሰራው ሌላው ኮድ 4-16021 ዳዎ ባስ ግን ጌጁ የማይሰራ ሲሆን ለማሰራትም ወደ ካምፓኒው በተደጋጋሚ ቢላክም እቃው ማለትም ስፔር ፓርቱ ባለመገኘቱ ከውጪ እስከሚመጣ ጠብቁ ተብለን እየጠበቅን እንገኛለን።

7. <u>ልዩ ልዩ፣</u>

7.1 <u>የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ላይ እርምጃ አወሳሰድ፣</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምሰት አንቀጽ 17/3 መሰረት ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሀሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን

እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው። በዚሁ መሰረት የ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ መወሰዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

ከዩኒቨርሲቲው ጋር የግንባታ ውላቸውን አቋርጠው ስለወጡ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ፣

- አህመድ መሀመድ የስራ ተቋራጭ (Dormitory(Do-T3-216) and (Dormitory-T3-217)፤ የውል መጠን ብር 7,527,167.31 ከዩኒቨርሲቲው ጋር የነበረው ውል የተቋረጠ ቢሆንም በውሉ ልዩ ሁኔታ በተቀመጠው እና በአማካሪው ድርጅት በአኪዩት ኢንጅነሪንግ(payment up on Termination) ተሰልቶ በተቀመጠው መሰረት ብር 594,484.24 ያልተቀጣ መሆኑ፤
- ሀብቴ ሀገጎ የግንባታ ስራ ተቋራጭ Dormitory-T1(Do-T3-236) and፣ Dormitory-(Do-237) የውል መጠን ብር 7,444,680.27 ከዩኒቨርሲቲው ጋር የነበረው ውል የተቋረጠ ቢሆንም በውሉ ልዩ ሁኔታ በተቀመጠው እና በአማካሪው ድርጅት በአኪዩት ኢንጅነሪንግ (payment up on Termination) ተሰልቶ በተቀመጠው መሰረት ብር 649,931.58 ያልተቀጣ ሲሆን፤

  ሁለቱ ድርጅቶች በድምሩ ብር 1,244,415.82 በውሉ መሠረት ያልተቀጡ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው በቋሚ ቅጥር መያዝ የሚገባቸውን የአስተዳደር የስራ መደቦች በአካዳሚክ /በመምህራን/ በተደራቢነት እንዲያዝ በማድረጉ በበጀት ዓመቱ ውስጥ አላግባብ የደመወዝ፣ የአኗላይዜሽን፣ የቤት ክራይ አበልና የኃላፊነት አበል በድምሩ ብር 57,105.28 ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ መሆኑ እና መመሪያውን መሠረት ያደረገ እንዲሆን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፤

የኦዲት አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ያልተውሰደ መሆኑ ታውቋል።

7.2. ስጋት፣

በኦዲት በሚሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት ዩኒቨርሲቲው የእርምት እርምጃ የማይወስድ ከሆነ በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ዘንድ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን አይቻልም፡፡ የመንግሥት ገንዘብና ንብረትም እንዲመዘበር መንገድ ይከፍታል፡፡

7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር በኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም በ2008 በጀት ዓመት በኦዲት በተሰጡ አስተያየቶች መሠረት የእርምት እርምጃ ተወስዶ ሪፖርት እንዲቀርብ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

7.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በኦዲተሮች በሚሰጡ አስተያየት መሰረት ማስተካከያዎችን በማድረግ ድክመቶችን ለማረም ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ድክመቶች እንዳይከሰቱ የምንሰራ ሲሆን ሁለቱ ኮንትራክተሮች ክስ ከመመስረቱ በፊት በውሉ መሰረት በግልግል ዳኝነት የሚታይ በመሆኑ በሂደት ላይ ነው፣ እንዲሁም በአካዳሚክ የተያዙ ቦታዎች በአሁኑ ሰአት ሙሉ በሙሉ በአስተዳደር ሰራተኞች ተመድበው ማስተካካያ ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገው የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!!